DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

ይህ፣ በትምህርት-ገበታ ላይ-መገኘት እና ያለማቋረጥ-የመቅረት ፖሊሲ (Attendance and Truancy Policy)፤ ከዚህ ቀደም በዚህ ጉዳይ ላይ፣ በDCPS ታውጆ የነበረውን ሁሉንም ፖሊሲ፣ ሜሞራንዳ (memoranda)፤ እና/ወይም መመሪያ የሚሰርዝ እና የሚተካ ነው።

**ቻንስለሩ ያጸደቁት:** box SIGN 15Q6WKVW-4ZZJW5WL **በስራ-ላይ የዋለበት ቀን:** ኦገስት (August) 25 ቀን 2025

# በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት እና ያለማቋረጥ-የመቅረት ፖሊሲ (Attendance and Truancy Policy)

## I. ዓላማ እና የስፋት-መጠን/SCOPE

የኮሎምብያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (The District of Columbia Public Schools (DCPS) ተልዕኮ፣ ተማሪዎችን - በሚያሳድጋቸው አካባቢ-ውስጥ - ጠንከር-ብለው በተሰጡ እና አስደሳች-በሆነ የትምህርት ተሞክሮዎች ውስጥ ሆነው፣ ወደ ሙሉ አቅማቸውን እንዲደርሱ ማድረግ ነው። DCPS እና ትምህርት ቤቶቹ፤ ወደዚህ ተልዕኮው/mission ለመስራት እንዲችሉ፣ በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት (attendance)ን እንደ አንድ ቁልፍ-የሆነ ሜትሪክስ/metrics ይመለከቱታል። በትምህርት-ገበታ ላይ የመገኘት ፓተርኖች (Attendance patterns) - በልጁ ዕድገት ላይ ተጽዕኖ በሚያደርጉ፣ ሌሎች ጎራዎች ላይ ተሞክሮዎች እንዲኖሩ፣ ቁልፍ-እይታዎችን የሚሰጥ ነው።

ይህ ፖሊሲ፤ አጠቃላይ - የትምህርት-ገበታ ላይ የመገኘት (attendance) መስፈርቶችን፣ በትምህርት-ገበታ ላይ በመገኘት-ላይ በትምህርት ቤት ስለሚጠበቁ-ነገሮች፣ ፈቃድ-ያገኘ መቅረቶች (excused absences) እና አስፈላጊ-የሆኑ ሰነዶችን፣ ክትባት እና በትምህርት-ገበታ የመገኘት (attendance) መስፈርቶችን፣ በትምህርት ቤት ስፖንሰር-በሆኑ እንቅስቃሴዎች ምክንያት፤ የሚደረጉ መቅረቶች (absences)ን፣ በትምህርት ቤት ላይ መሠረት ያደረጉ የትምህርት-ገበታ ላይ የመገኘት ጣልቃ-ገብነቶችን፣ በተደጋጋሚ-ከመቅረት (absenteeism) ጋር ተዛማጅ-የሆኑ፣ የተከለከሉ እርምጃዎች፣ ለደረጃ-አሰጣጥ እና ለማለፍ በትምህርት-ገበታ ላይ የመገኘት (attendance) መስፈርቶችን፣ ለሁለተኛ-ደረጃ ተማሪዎች-አርፍዶ ትምህርት ቤት መድረስ፣ ቀደም-ብሎ መለቀቅ (early dismissal) - ለሁሉም ተማሪዎች፣ እና በትምህርት-ገበታ የመገኘት መዝገብ ላይ አቤቱታዎችን-ማቅረብን - ይዘረዝራል።

ይህ ፖሊሲ፣ ከዚህ ቀደም በዚህ በሚመለከተው ጉዳይ ላይ፣ በDCPS ታውጆ የነበረውን ሁሉንም ፖሊሲዎች፣ ሜሞራንዳ (memoranda)፣ እና መመሪያ የሚሰርዝ እና የሚተካ ነው።

## II. ሥልጣን እና በስራ-ላይ የሚውል ሕግ[1]

| **ምንጭ/Source** | **ጥቅስ (Citation)** |
|---|---|
| የፌደራል ሕግ | - የቤተሰብ ትምህርታዊ መብቶች እና የግላዊነት ድንጋጌ/Family Educational Rights and Privacy Act (FERPA), 20 U.S.C. § 1232g |
| የፌደራል ደንቦች | - የ'FERPA' የማስፈጸሚያ ደንቦች (implementing regulations)፣ 34 C.F.R. Part 99 |
| የኮሎምብያ ዲስትሪክት ሕግ | - D.C. Official Code § 38-202 – የትምህርት ቤት በትምህርት-ገበታ የመገኘት (attendance) መስፈርቶች አመሰራረት<br>D.C. Official Code § 38-236.04 – እንዳይገኙ መከልከል (exclusion)ን እንደ የስነ-ስርዓት መቅጫ እርምጃ አድርጎ መጠቀምን-ውሱን ማድረግ<br>D.C. Official Code § 38-501, et seq. – የትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ ክትባት (Immunization) |
| የኮሎምብያ ዲስትሪክት የማዘጋጃ ቤት ደንቦች | የስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (Office of State Superintendent of Education)<br>- 5-A DCMR § 2100 – አጠቃላይ ደንቦች/General Provisions<br>- 5-A DCMR § 2101 – በትምህርት-ገበታ ላይ የመገኘት መዝገቦች እና ሪፖርት-ማድረጊያ/Attendance Records and Reporting - 5-A DCMR § 2102 – መቅረቶች/Absences<br>- 5-A DCMR § 2103 – የቀሪዎች ጣልቃ-ገብነት (Absentee Intervention) እና በትምህርት ቤት መሠረት-ያደረገ የተማሪ እርዳታ ቡድኖች<br>- 5-A DCMR § 2199 – ትርጓሜ (Definitions)<br>የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች<br>- 5-B DCMR § 2103 – ያለማቋረጥ-መቅረት (Truancy)<br>ዋናው/ኦሪጅናል ታይትል (Original Title) 5<br>- 5-E DCMR § 2101 – መቅረቶች (Absences) |

[1] በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ያለ ምንም-ነገር፣ የፌደራል፣ ስቴት፣ ወይም የአካባቢው (local) ሕግን - አይተካም።

| | |
|---|---|
| | - 5-E DCMR § 5300 – የሕዝብ ትምህርት ቤት የክትባት (Immunization) ሂደቶች እና መስፈርቶች |

## III. ቁልፍ-የሆኑ አባባሎች እና ትርጉሞቻቸው

***መቅረት* (Absence)** ማለት፤ በትምህርት ቀን ውስጥ - ተማሪው ሙሉ-በሙሉ ወይም በከፊል በሚቀርበት-ጊዜ ማለት ነው።[2] DCPS ፈቃድ-ባገኘ (excused) እና ፈቃድ-ባላገኘ (unexcused) መቅረቶች/absences መካከል፣ ልዩነቶችን-ይፈጥራል።

**በተደጋጋሚ-መቅረት (Absenteeism)** ማለት፤ ከፍተኛ ተደጋጋሚነት ያለው የመቅረት ፓተርን (pattern) ማለት-ነው።[3]

**ከመደበኛ-ውጪ የሚከናወን የርቀት የትምህርት-አሰጣጥ (Asynchronous Distance Instruction)** ማለት፤ ጎን-ለጎን በሆነ መንገድ የማይሰጥ (non-simultaneous) የርቀት ትምህርት-አሰጣጥ ሲሆን፣ አስተማሪው በእውነተኛ-በዚያኑ ጊዜ (real time) የሚሰጥ የትምህርት አሰጣጥ ሳይኖር-ተማሪው ለብቻልው ስራውን ሰርቶ-የሚያጠናቅቅበት ማለት ነው።[4]

**በትምህርት-ገበታ ላይ በመገኘትና-አለመገኘት ላይ - የእርምጃ ዕቅድ (Attendance Action Plan)** ማለት፤ አንድን-ግለሰብን እና የተማሪውን በልዩ ሁኔታ የሚያስፈልጉትን ሊያሟላ እንዲችል ተደርጎ የተቀረጸ የጽሁፍ-ሰነድ እና፣ የተማሪውን አስፈላጊ የሆኑ በትምህርት ገበታ መገኘት (attendance) ሰነድን ዝርዝር የያዘ፣ የሚጠበቀውን የትምህርት ገበታ ላይ መገኘት (attendance) ግቦችን፣ በትምህርት ቤት ላይ መሠረት ያደረገ ወይም ሦስተኛ-ወገን/third-party-አገልግሎት ሰጪ-የሆነን ጣልቃ-ገብነቶች - በትምህርት ቤት ውስጥ መሠረት ባደረገው የተማሪ እርዳታ ቡድኑ አማካኝነት በተወሰነው - ፈቃድ-ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረቶች (unexcused absences) ላይ -ይህን ችግር ፈጣሪ የሆኑትን ችግሮች መፍትሄ በማስገኘት ላይ የሚያገለግል ማለት ነው።[5]

**በትምህርት-ገበታ የመገኘትና-አለመገኘት ካውንስለር/ተወካይ (Attendance Counselor/Designee)** ማለት፤ በርዕሰ መምህሩ - የሚከተሉትን ኃላፊነቶች እንዲወጣ የተመደበ አንድ-ሰው(ዎች) ሲሆኑ፤ የተማሪዎችን በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት (attendance)ን ለማሻሻል፣ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በመደበኛ ሁኔታ መገኘታቸውን ማረጋገጥ፣ የተማሪውን በትምህርት ገበታ ላይ መገኘትን ለመጨመር እና በመቅረት ላይ ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ - የትምህርት ገበታ ላይ መገኘት ጣልቃ-ገብነቶች/interventionsን ለማስተባበር እና ለመከታተል የሚመደብ-ሰው/ዎች ማለት ነው።

**የትምህርት-ገበታ መገኘትና-አለመገኘት ተቆጣጣሪ (Attendance Monitor)** (የትምህርት ገበታ/attendance የግንኙነት-ተወካይ (point-of-contact (POC) ተብሎም ይታወቃል) ማለት፤ በትምህርት ተቋሙ ርዕሰ መምህር፣ በሚከተሉት ላይ ኃላፊ እንዲሆን የተመደበ ሰው(ዎች) ማለት ሲሆን፤ ለኮሎምብያ ዲስትሪክት ለትምህርት እና የትምህርት ቤት በትምህርት-ገበታ መገኘት ሕጎችና፣ ደንቦች እና የOSSE ፖሊሲዎች - በግዳጅ ማሟላት የሚያስፈልጉትን -በእያንዳንዱ የትምህርት ተቋም ውስጥ ገብቶ ለሚማር ተማሪ - የትምህርት ገበታ ሰነዶችን - መሰብሰብ፣ መጠበቅ እና ሪፖርት የሚያደርግ ግለሰብ/ቦች ማለት ነው።[6]

**ስር-የሰደደ ተደጋጋሚ-መቅረት (Chronically Truant)** ማለት፤ አስገዳጅ ዕድሜ ውስጥ ለሆነ ተማሪ - አስር (10) ወይም ከዚያ በላይ ቀናቶችን፣ ፈቃድ-ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረቶች - በአንድ የትምህርት-ዓመት ውስጥ የሚገኝበት-ሁኔታ ማለት ነው።[7]

***ፈቃድ-ያገኘ መቅረት* (Excused Absence)** ማለት፤ በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ከተገለጹት-ውስጥ - ተቀባይነት-ያለው የፈቃድ-ማግኛ ዓይነቶች ውስጥ-አንዱ ነው። መቅረቱን - “ፈቃድ-ያገኘ/excused” ለማድረግ፣ የወላጅ/አሳዳጊ ፈቃድ-ብቻ፤ በቂ-አይደለም። መቅረቶች (Absences)፣ ፈቃድ-ሊያገኙ የሚችሉት፣ የDCPS ፖሊሲ መስፈርቶችን የሚያሟላ-ከሆነ ብቻ ይሆናል።

**ሙሉ የትምህርት ቀን** ማለት፤ አጠቃላይ የትምህርት አሰጣጥ ሰዓታቶቹ በመደበኛነት በአንድ የትምህርት-ቀን ውስጥ የሚሰጠው-ማለት ነው።[8]

---

2 *በ*5-A DCMR § 2199.1 ላይ ተመልከቱ።
3 *በ5-A DCMR § 2199.1* ላይ ተመልከቱ።
4 *በ*5-A DCMR § 2199.1 ላይ ተመልከቱ።
5 *በ*5-A DCMR § 2199.1 ላይ ተመልከቱ።
6 *በ*5-A DCMR § 2199.1 ላይ ተመልከቱ።
7 የዲሲ ህጋዊ ኮድ/D.C. Official Code § 38-202(a); በ5-A DCMR § 2199.1 ላይ ተመልከቱ።
8 *በ*5-A DCMR § 2199.1 ላይ ተመልከቱ።

**ሙሉ-ለሙሉ መቅረት (Fully Absent)** ማለት፤ ለተመደበው የትምህርት ቀን፣ ተማሪው - ለአጠቃላይ የትምህርት-አሰጣጥ ቀኑ - በትምህርት-ገበታ ላይ በማይገኝበት ጊዜ፤ ማለት ነው። ይህ ስያሜ፤ ለሁለቱም - ፈቃድ-ላገኘው (excused) እና ፈቃድ-ላላገኘው (unexcused) - ለሙሉ የትምህርት ቀኑ መቅረቶች፤ በስራ-ላይ የሚውል ነው።[9]

**ሙሉ-ለሙሉ መገኘት (Fully Present)** ማለት፤ ለተመደበው የትምህርት ቀን፣ ተማሪው - ለአጠቃላይ የትምህርት-አሰጣጥ ቀኑ - በትምህርት-ገበታ ላይ በሚገኝበት ጊዜ፤ ማለት ነው።[10]

**በቦታው-ላይ መገኘት (In-Seat Attendance)** ማለት፤ በትምህርት ቤት ተመዝግቦ ተማሪው - የተገኘበት ቀናት - በ'መቶኛ/percent' ሲሰላ-ማለት ነው።

**ሞጁል (Module)** ማለት፤ የትምህርት-አሰጣጥ ቀኑ ንዑስ ክፍል (subdivision) ሲሆን፣ እንደ የመማሪያ ክፍለጊዜ (class period) ወይም ለትምህርታዊ-ሂደት የተገደበ፤ ማለት ነው።[11]

**'MTSS'** ማለት፤ 'a multi-tiered system of supports' ለትምህርት-ሰጪዎች፣ የትምህርት ቤት አመራሮች፣ እና የዲስትሪክት መሪዎች - ያሏቸውን በመማር ላይ ያሉትን እንቅፋቶች - በዘዴዎች ደረጃ (systems level) ለማስወገድ፣ ማስረጃ-ላይ መሠረት ያደረጉ ልምምዶችን በአጠቃላይ ልጁን ከ' tiered continuum' ጋር ለመርዳት ጥቅም-ላይ የሚውል፣ እና በመረጃ-ስብስብ ላይ መሠረት ያደረጉ - ዒላማ-ለተደረገለት እና ጠንከር-ብሎ ለሚሰጡ  የጣልቃ-ገብነቶች ውሳኔዎችን ለመውሰድ የሚያገለግሉ-ማለት ነው።

**የMTSS የአመራርነት ቡድን/Leadership Team** ማለት፤ በትምህርት ቤት ውስጥ - 'MTSS'ን የሚመሩ - የሥራተኛ አባላቶች ቡድን ነው። ይህ ቡድን፤ ርዕሰ መምህር፣ ረዳት ርዕሰ መምህር፣ ካውንስለር፣ ማህበራዊ-ሠራተኛ (social worker)፣ የስነ-ልቦና ባለሞያተኛ/psychologist፣ የትምህርት ቤት ነርስ፣ አስተማሪዎች፣ የልዩ-ትምህርት ሠራተኛ/special education staff፣ የትምህርት-ገበታ መገኘት ካውንስለር/attendance counselor፣ ወይም የትምህርት-ገበታ መገኘት ተወካይ/attendance designeeን ሊያካትት-ይችላል።

**ውጤት (Output)** ማለት፤ በተማሪው የርቀት ትምህርት አሰጣጥ ሞጁል ወቅት የተጠናቀቀውን እንቅስቃሴ - በዚያ ሞጁሉ ውስጥ የተሰጠውን የትምህርት-አሰጣጥ የሚያንጸባርቅ ማለት ነው።[12]

**ወላጅ (Parent)** ማለት፤ ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ወይም ሌላ ሰው በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ የሚኖሩ-እና የማሳደግ-ኃላፊነት ወይም የታዳጊ-ልጁ (minor) ቁጥጥር የተሰጠው-ሰው ማለት ነው።[13]

**በከፊል መቅረት (Partially Absent)** ማለት፤ የትምህርት ቀን ተብሎ በተሰየመው ቀን፣ ተማሪው - ከ60 በመቶ ባነሰ ጊዜ ለትምህርት-አሰጣጥ ቀኑ በሚገኝበት-ጊዜ፤ ማለት ነው። ይህ፤ ለሁለት - ፈቃድ-ላገኘው (excused) እና ፈቃድ-ላላገኘው (unexcused) መቅረት/absence፤ በስራ-ላይ ይውላል።[14]

**በከፊል መገኘት (Partially Present)** ማለት፤ የትምህርት ቀን ተብሎ በተሰየመው ቀን፣ ተማሪው - ከ60 በመቶ ባነሰ ጊዜ - የቀረበት-ክፍለ ጊዜ ፈቃድ-ያገኘ የነበረ (excused) ሆነም-አልሆነ፤ ለትምህርት-አሰጣጥ ቀኑ በሚገኝበት-ጊዜ፤ ማለት ነው።[15]

**መገኘት (Present)** ማለት፤ በትምህርት ቀን ውስጥ - ተማሪው ሙሉ-በሙሉ ወይም በከፊል - በሚገኝበት-ጊዜ፤ ማለት ነው።[16]

**ተገልሎ-መቆየት/ኳራንቲን (Quarantine)** ማለት፤ በአካል-ተገኝቶ ከሚሰጠው የትምህርት አሰጣጥ ውስጥ እና ከሌሎች እንቅስቃሴዎች ውስጥ፤ ከኮሎምቢያ ዲስትሪክ ባለስልጣናት ትዕዛዝ መሠረት - ባለው ተላላፊ በሽታ፣ ብክለት (infection)፣ ተወርሮ-መበከል (infestation)፣ ወይም ሌላ ከሌሎች ተማሪ በሕክምና ወይም ለጤና ምክንያቶች መለየት የሚገባው ሁኔታ ሲፈጠር፤ ተገልሎ-የሚለይበት ሁኔታ፤ ማለት ነው።[17]

---

9 /5-A DCMR § 2199.1 ላይ ተመልከቱ።
10 /5-A DCMR § 2199.1 ላይ ተመልከቱ።
11 /5-A DCMR § 2199.1 ላይ ተመልከቱ።
12 /5-A DCMR § 2199.1 ላይ ተመልከቱ።
13 /5-A DCMR § 2199.1 ላይ ተመልከቱ።
14 /5-A DCMR § 2199.1 ላይ ተመልከቱ።
15 /5-A DCMR § 2199.1 ላይ ተመልከቱ።
16 /5-A DCMR § 2199.1 ላይ ተመልከቱ።
17 *[5-A DCMR § 2102.2(b)]* ላይ ተመልከቱ።

**የዘወትር የርቀት የትምህርት አሰጣጥ (Routine Distance Instruction)** ማለት፤ የርቀት የትምህርት አሰጣጥ/distance instructionን በትምህርት ቤት - በመደበኛነት ወይም በሌላ ሊገመት-በሚችል፣ የአስቸኳይ-ጊዜ ባልሆነ/nonemergency አሰራር - ጥቅም-ላይ የሚውል ማለት-ነው።[18]

**ሁኔታዎችን ያገናዘበ የርቀት ትምህርት (Situational Distance Learning)** ማለት፤ የተወሰነ-የጊዜ ገደብ ሆኖ ትምህርት-ቤቱ - አስገዳጅ በሆኑ ሁኔታዎች የትምህርት አሰጣጡን - በጊዜያዊ፣ የአስቸኳይ-ጊዜ ሁኔታ አስፈላጊነት ምክንያት መስጠት በሚከለክልበት ጊዜ፣ የመማሪያ-ክፍሉን፣ የክፍል-ደረጃን፣ ወይም አጠቃላይ ትምህርት ቤቱን ወደ የርቀት ትምህርት (distance learning) የሚያሸጋግርበት-ሁኔታ ማለት-ነው። እንዲህ-ዓይነቱ ሁኔታ፣ ቀደም-ተብሎ ያልታቀደን ነገር በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች (ለምሳሌ፤ በሕዝብ ጤና ምላሽ መስጠት፣ በክንውናዊ ጉዳዮች፣ አስቸጋሪ-የሆነ የአየር-ጠባይ) ምክንያት ምላሽ-ሊሰጥበት የሚያስፈልግ ይሆናል። ትምህርት ቤቱ እንደነዚህ ያሉ የአስቸኳይ ጊዜ የክንውናዊ ሁኔታዎች መኖራቸውን ከወሰነ - የትምህርት ቤት አመራሮች የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው: ለውጡን-ለማድረግ ከትምህርት አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጁ ፈቃድ-ማግኘት አለባቸው፤ (በርዕሰ-መምህሩ የስልጣን-ደረጃ ውስጥ ለሆኑ የክፍል-ደረጃዎች ዝውውሮች ካልሆነ-በስተቀረ) እና፣ አንድ-ጊዜ ፈቃዱን ካገኙ በኋላ፣ ወዲያውኑ ወላጆችን እና ሠራተኞችን - በርቀት ትምህርት ላይ ስለተደረገው ሁኔታዊ-የሆነ ለውጥ ያሳውቃሉ። የትምህርት ቁሳቁሶች/materialsን በበቂ-ሁኔታ ተማሪዎች - ለማግኘት የሚችሉ-መሆናቸውን፤ ርዕሰ-መምህራኖች ማረጋገጥ-አለባቸው።

በሁኔታዊያዊ የርቀት መማር (situational distance learning) ውስጥ - ተማሪው ተገኝቷል/present ብሎ ከግምት-ውስጥ ለማስገባት፣ ትምህርት ቤቱ የሚከተሉትን ማድረግ-ለበት:

1. የተማሪውን መገኘት፤ ትክክለኛነት ማረጋገጥ። ይህ በበርካታ ዓይነት መንገዶች መከናወን የሚችል-ይሆናል፤ ለምሳሌ፣ ተማሪው ወደ መማሪያ መቆጣጠሪያ ዘዴው - በማንኛውም የግንኙነት/communication መንገዶች- (ለምሳሌ - ቴክስት/text፣ ስልክ፣ ካሜራ) ባሉት አማካኝነት መግባቱን በማረጋገጥ፤ እና
2. በየሁኔታዊያዊ የርቀት መማር ቀኑ (situational distance learning day) በቀረበው-መሠረት፤ ቢያንስ አንድ (1) ወይም ከዚያ-በላይ የሆነውን - የቤት/ክፍል ስራ/assignment፣ ስራ/task ወይም ሌላ ዓይነት የቀለም-ትምህርት ውጤት/outputን - ተማሪው ሰርቶ-ማጠናቀቁን ማረጋገጥ።

**መደበኛ ባልሆነ-መንገድ የሚሰጠውን ትምህርት (Synchronous Learning)** ማለት፤ የቀለም-ትምህርት አቀማመጥ ሆኖ - ማስተማር እና መማሩ የሚካሄደው ወዲያውኑ-ጎን ለጎን ሆኖ በሚሰጥ ሁኔታ (simultaneously) ይኸውም፣ አስተማሪው በዚያኑ ጊዜ - እርምጃ መውሰድ እና ምላሽ መስጠት የሚችልበት ሲሆን - ተማሪዎችም እንደዚሁ በዚያኑ ጊዜ እንደዚሁ ለማድረግ የሚችሉበት ሁኔታ ነው።[19]

**የተማሪ በትምህርት ገበታ ላይ መገኘና አለመገኘት ኮንፈረንስ (Student Attendance Conference)** (SAC) ማለት፤ ስብሰባው በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት ካውንስለር (Attendance Counselor)/ወኪል (Designee)፣ ወላጅ/አሳዳጊ፣ እና በተማሪ (እንደ አስፈላጊነቱ) ጋር፣ ግለሰብ ተማሪውን የትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት የእርምጃ ዕቅዶችን በማዘጋጀት እና በማስፈጸም፣ እና የጣልቃ-ገብነት ስልቶችን - በትምህርት ቤት ወይም በማህበረሰብ-ላይ ያተኮረውን ለማካሄድ፣ እና እና የተማሪውን ስኬታማነት ለማሳደግ የተቀረጸውን በማረብ ተማርውን ለመርዳት የሚደረግ ነው።[20] 'SAC'፤ በአካል-ተገኝቶ ( in-person) - በስልክ-አማካኝነት፣ ወይም በቪዲዮ ኮንፈረንስ-አማካኝነት ሊካሄድ ይችላል። እነዚህ ስብሰባዎችም፤ እንደ - 'የተማሪ እርዳታ ቡድን (Student Support Team (SST)' ስብሰባዎች ሆኖ ሊመራ/referr ሊሆን ይችላል።

**ፈቃድ-ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረቶች (Unexcused Absence)** ማለት፤ በተመደበው ቀን ላይ ተማሪው በሙሉ-ቀን መቅረት ወይም በከፊት-በመቅረት፤ ምንም-ሕጋዊ የሆነ ምክንያት ሳይኖረው፤ መቅረት ማለት-ነው።[21]

## IV. መስፈርቶች

### A. አጠቃላይ - የትምህርት-ገበታ ላይ የመገኘት (Attendance) መስፈርቶች

በአሁኑ የትምህርት ዓመት ውስጥ - ከሴፕቴምበር (September) 30 ቀን በፊት - ዕድሜያቸው አምስት (5) ዓመት የሞላቸው ሁሉም ልጆች፤ ለትምህርት ዕድሜያቸው የደረሰ ተብለው ከግምት-ውስጥ የሚገቡ እና በየቀኑ ወደ ትምህርት ቤት ተገኝተው እስከ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

---

18 በ5-A DCMR § 2199.1 ላይ ተመልከቱ።

19 በ5-A DCMR § 2199.1 ላይ ተመልከቱ።

20 በ5-A DCMR § 2103.4 እና D.C. Official Code § 38-201(3B) ላይ ተመልከቱ። 'SAC' - በትምህርት ቤት መሠረት-ያደረገ የተማሪ-እርዳታ ቡድን ኃላፊነቶችን - የሚያሟላ-ነው።

21 በ5-A DCMR § 2102.1 ላይ ተመልከቱ።

የምርቃት (Graduation) መስፈርቶች እስከሚደርሱ ድረው፤ ወይም እስከ 18 የልደት-በዓላቸው ድረስ መማር አለባቸው።[22,23] አንድ-ጊዜ በቅድመ-መዋዕለሕፃንት (Pre-K) ተማሪዎች እንደ የDCPS ተማሪዎች ሆነው ከተመዘገቡ - እንደ ማንኛውም ለትምህርት-የደረሱ ትተማሪዎች አንድ-አይነት በሆነ ሁኔታ በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት ፖሊሲዎች (attendance policies)ን - ሰዓቱን-ጠብቆ በትምህርት ቤት ውስጥ መገኘትን ጨምሮ ህጉን መከተል-ይጠበቅባቸዋል።

ከከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት የተመረቁ፣ ለአቅመ-አዳም ያልደረሱ (Minors)፤ ከዚያ በኋላ በትምህርት ቤት ውስጥ ገብተው መማር አያስፈልጋቸው።።[24] ዕድሜአቸው አስራ-ሰባት (17) ለሆኑ፣ በጊዜው-ለመመረቅ በትክክለኛው-መንገድ ላይ ለሚገኙ፣ እና ጥቅም-ሊገኝበት የሚችል ቅጥር/employment ላይ በመደበኛነት ሰነዶችን-ለማቅረብ የሚችሉ ተማሪዎች፤ ተለዋዋጭነት-ያለው የትምህርት ቤት ሰዓታት (Flexible school hours) ይፈቀድላቸዋል።[25]

### B. ከትምህርት ቤት የሚጠበቁ-ነገሮች/School Expectations

ሁሉም ትምህርት ቤቶች፤ የተለየ ፕሮቶኮልን - በትምህርት ገበታ ላይ መገኘትን (attendance) እና ተደጋጋሚ-መቅረቶችን (absenteeism) ለመቆጣጠር - ፈቃድ-ያላገኙ ከትምህርት-ገበታ መቅረቶች (unexcused absences)ን በመከላከል-ላይ ትኩረት ማድረግ እና የተማሪዎችን ፍላጎቶች ምላሽ-ለመስጠት የቀለም-ትምህርት እና የባህሪያዊ ጣልቃ-ገብነቶችን በማካሄድ ላይ ትኩረት ማደረግን ጨምሮ - ማስፈጸም-አለባቸው። የትምህርት ቤት ሠራተኛ-ሹሞች፤ በትምህርት ገበታ-ላይ የመገኘት ቁጥጥርን በትክክለኛነት በየቀኑ በመውሰድ - በተማሪው የመረጃ ዘዴ (student information system (SIS) ውስጥ በትክክል ማስገባት ወይም በDCPS በቀረቡ አማራጭ-መንገዶች አማካኝነት ማስገባት አለባቸው። የትምህርት-ገበታ ላይ መገኘትን በመረጃ-ለመመዝገብ - ተጨማሪ መስፈርቶች፣ እና ለርቀት የመማር ሞዴሎች - በትምህርት-ገበታ ላይ ስለመገኘት የሚጠበቁትን ነገሮች፤ በAppendix A ቀርበዋል።

የትምህርት ዓመቱ ከመጀመሩ-አስቀድሞ፣ የሁሉም ትምህርት ቤት ርዕሰ-መምህራኖች - በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘትና አለመገኘት የግንኙነት-ተወካይ (point-of-contact (POC) የሆነን ሰው መወከል-አለባቸው። በDCPS የ'Central Services Attendance Team' ትዕዛዝ -መሠረት፤ በትምህርት ገበታ ላይ መገኘትና አለመገኘት የግንኙነት-ክፍል ሠራተኛ (attendance POC) - በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት (Attendance) መዝገቦችን ጊዜውን በጠበቀ መልኩ ማስገባት፣ ማንኛውም የተስተካከለ በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት (Attendance) መዝገቦችን በአስራ-አምስት (15) የስራ-ቀናቶች ውስጥ ማስገባት፣ እና ስለገቡት በትምህርት ገበታ ላይ ስለመገኘት ሰነዶች ላይ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ጊዜውን-በጠበቀ መንገድ ምላሾችን መስጠት አለባቸው።

የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራኖች፤ የትምህርት-ገበታ ተወካይ የሆነን ሰው (attendance designee) - የተማሪዎችን በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት (attendance)ን ለማሻሻል፣ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በመደበኛ ሁኔታ መገኘታቸውን ለማረጋገጥ፣ የተማሪውን በትምህርት ገበታ ላይ መገኘትን ለመጨመር እና በመቅረት ላይ ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ - በዚህ ፖሊሲ የሚያስፈልገውን - የትምህርት ገበታ ላይ መገኘት ጣልቃ-ገብነቶች/interventionsን ለማስተባበር እና ለመከታተል ይህን-ተወካይ መመደብ-አለባቸው። ትምህርት ቤቱ - በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት ካውንስለር (attendance counselor) ካለው፤ የትምህርት-ገበታ ላይ ተወካይ (attendance designee) የስራ-ድራሻን በተልምዶ-የሚያከናውኑ ሲሆን (በዚህም-ምክንያት፤ ይህ የስራ ድርሻ በዚህ ፖሊሲ ውስጥ እንደ 'Attendance Counselor/Designee፣ ወይም AC/AD ተብሎ ተጠቅሷል)፤ ሆንም-ግን አስፈላጊ አይደለም። እንደ በትምህርት-ገበታ የመገኘት የግንኙነት ሠራተኛ (attendance POC) ሆኖ ተለይቶ-የተመደበው ግለሰብ፤ እንደ 'AC/AD' በመሆንም - እነዚህ ኃላፊነቶችም ሊኖሩት ይችላል።

በመጀመሪያ-ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ አስተማሪዎች፣ ዕለታዊ በትምህርት-ገበታ መገኘትን መውሰድ እና ማስገባት ያለባቸው፣ እና በሁለተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ-የሚገኙ አስተማሪዎችም በየእያንዳንዱ ክፍለ-ጊዜ/period ወቅት - በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘትን መውሰድ እና በአስፐን/Aspen ማስገባት ያስፈልጋቸዋል። ወደ ትምህርት ቤት ህንፃው ወይም የመማሪያ-ክፍሉ ውስጥ - ዘግይቶ የገባ ማንኛውም ተማሪ፤ በአስፐን (Aspen) ውስጥ እንደ አርፋጅ (as tardy) ሆኖ-የሚመዘገብ፣ እንጂ እንደ ቀሪ ሆኖ አይመዘገብም። በትምህርት ገበታ-ላይ መገኘትና አለመገኘት (Attendance)፤ የትምህርት ቀኑ ከማለቁ-በፊት፣ በትክክል-ገብቶ መጠናቀቅ እና አዲሱ መረጃ እንደታወቀ፤ በየቀኑ-አዲስና-ማሻሻያ (update-መደረግ) አለበት።

### C. ፈቃድ-ያገኘ መቅረቶች (Excused Absences) እና አስፈላጊ-የሆኑ ሰነዶች

መቅረቱ/absence -ፈቃድ እንዲያገኝ ለማድረግ፤ በተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ፣ ወይም አዋቂ-በሆነው ተማሪ/adult student (ማለትም፤

---

22 የD.C. Official Code § 38-202 አስገዳጅ-በሆነ የተማሪዎች ዕድሜ፣ በመደበኛነት በትምህርት ገበታ መገኘት መስፈርትን፤ ተመልከቱ። መደበኛ-በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት/Regular attendance - የሚያካትተው፤ ወደ ትምህርት ቤት በሰዓቱ-መድረስንም ነው።

23 የ5-E DCMR § 3002.1(d)ን በመከተል፤ ለልዩ ትምህርት (special education) በDCPS ብቁ-ሆኖ የተገኘ ልጅ፤ እስከ ሴሚስተሩ መጨረሻ - ዕድሜያቸው 22 እስከሚሆን ድረስ፤ አገልግሎቶችን ለማግኘት ብቁ-ይሆናል።

24 D.C. Code Official Code § 38-202(b).

25 D.C. Official Code § 38-202(b) ተመልከቱ። ተቀጣሪ-ለሆኑ ተማሪዎች፤ የግማሽ-ቀን የጊዜ ሰሌዳዎችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፤ በ5-B DCMR § 2103.2 እና በ5-E DCMR § 2101.2 ላይ ተመልከቱ።

18 ዓመት ወይም ከዚያ-በላይ ዕድሜው የሆነ)፣ ከሁለት-አንዱን:

- የቀኑን-በከፊል ወይም የሙሉ-ቀን መቅረቱ (absence) ከመፈጸሙ-አስቀድሞ፤ ወይም
- በ'አምስት (5)' የትምህርት ቀናት - ተማሪያችሁ ይህን-የከፊል ወይም የሙሉ-ቀን መቅረት - ካደረገ-በኋላ፣ ወይም ከተራዘመ-የትምህርት ቤት መቅረት-በኋላ፣ ወደ ትምህርት ቤት ሲመለስ፤ የጽሁፍ ወይም በኤሌክትሮኒክ-የገባ - ማስታወሻ/noteን፣ ለትምህርት ቤቱ ማቅረብ አለበት።[26]

ሁሉም-ተማሪዎች፤ በ504 plan ወይም በየየግል የትምህርት ፕሮግራም (Individualized Education Program (IEP) የተደገፉ-ተማሪዎችን ጨምሮ፤ እና ፈቃድ-ላገኘ መቅረት/excused absence - ሁሉም ማስታወሻዎች/notes፣ መስፈርቶቹን ማሟላት አለባቸው።

ከትምህርት ዓመት 2025-26 ጀምሮ፤ ፈቃድ-ያገኘ መቅረት/excused absenceን በሰነድነት-የሚያሳዩ ማስታወሻዎች/notes፤ በDCPS የወላጅ ፖርታል/Parent Portal[27] መግባት ወይም ለትምህርት ቤት በትምህርት-ገበታ መገኘት ሠራተኛ (attendance POC) ሊሰጥ-ይችላል። ሌሎች ሰነዶች (ማለትም፤ የሐኪም ማስታወሻ፣ የፍርድ-ቤት ሰነዶች፣ ወይም ሌላ ተዛማጅ-የሆኑ ድጋፍ-ሰጪ መረጃዎች) - በወላጅ ፖርታል (Parent Portal) ላይ ለመጫን/uploaded የማይችሉ፤ እና ወደ የትምህርት ቤት በትምህርት-ገበታ መገኘት ሠራተኛ (attendance POC) ሊቀርቡ-ይችላሉ። የወላጅ ፖርታል (Parent Portal) - ለሁሉም ትምህርት ቤቶች እና ቤተሰቦች መገኘት-የሚችል እና ዓላማ-ያደረገው ፈቃድ-መስጫ ማስታወሻዎች/excuse notesን ለማስገባት-ሂደቱ እንደ ማመቻቻ እና መጠቀሚያ-መንገድ ሆኖ እንዲያገለግል-ነው።

ተገቢ-የሆነ ማስታወቂያ እና ተጨማሪ ሰነድ - አስፈላጊ ለሆነ - በአምስት (5)-የትምህርት ቀን የጊዜ-ገደብ ውስጥ ከቀረበ፤ ትምህርት ቤቱ የቀረበትን ምክንያት እንደ ፍቃድ የተሰጠው እንደሆነ አድርጎ አስተካክሎ በ48 የስራ-ቀን ሰዓታት ውስጥ ማስተካከያ-ማድረግ አለበት።

ሁሉም የእጅ-የተፃፉ ማስታወሻዎች፤ የሚከተሉት መያዝ-አለባቸው:

1. ቀን-መፃፍ-አለበት፤
2. የመቅረቱ (absence)ን ምክንያት ያካተተ-መሆን፣ እና
3. ተማሪያችሁ፣ ከትምህርት ቤት ውጪ የነበረበትን፣ ወይም የሚሆንበትን ቀናቶች-በግልጽ መጥቀስና ማካተት። ከላይ የተጠቀሱትን - እነዚህን መስፈርቶች ያላሟሉ ማስታወሻዎች (Notes)፤ ከግምት-ውስጥ አይገቡም።

ሁሉም ተማሪዎች - የክፍል-ደረጃቸው ምንም-ሆነ ምን፣ 40% ወይም ከዚያ በላይ የሚሆነውን የትምህርት ቀን ሳይማሩ-ያመለጣቸው (ማለትም፤ በከፊት-ቀሪ የሆኑ) ለዚያ-ቀን የቀሩ-ሆነው ይወሰዳሉ። ፈቃድ-ለማግኘት፤ ይህን-መሰሉ መቅረት/absence - ማስታወሻ (note) ያስፈልገዋል።

በማንኛውም-ምክንያቶች፣ ከዚህ በታች በ[Section C.1](#) ውስጥ - የተዘረዘሩት መቅረቶች (Absences)፤ ፈቃድ-ያገኘ መቅረቶች (excused absences) ናቸው። ለአምስት (5) ወይም ከዚያ በላይ ተከታታይ ቀናቶች በማንኛውም-ምክንያት የሚከሰቱ መቅረቶች (Absences)፤ በ[Section C.2](#) ውስጥ እንደተዘረዘረው፤ ፈቃድ-ለማግኘት (excused-ለመሆን) ተጨማሪ ሰነዶችን ያስፈልጋሉ።

### 1. ፈቃድ-ያገኙ መቅረቶች (Excused Absences)

የሚከተሉትን መቅረቶች (absences) - ከወላጅ/አሳዳጊ ማስታወሻ ከገባ፣ ፈቃድ-ያገኘ መቅረት (excused absence)[28] ሆኖ ከግምት-ውስጥ ሊገባ የሚችለው፤ በSection C.2: ውስጥ - አስፈላጊ-ከሆነ፣ በሚያስፈልጉት ድጋፍ-ሰጪ ሰነዶች አማካኝነት - ፈቃድ-ሊያገኝ ይችላል:

- የተማሪ - ህመም። የሐኪም ማስታወሻ/doctor's note - ለተማሪው ለአምስት (5) ወይም ከዚያ-በላይ ተከታታይ-የሆኑ ቀናት መቅረት/absent - ያስፈልገዋል፤[29]
- እራሳቸው-ወላጅ ለሆኑ ተማሪዎች - ልጃቸው ሲታመምባቸው። የሐኪም ማስታወሻ/doctor's note - ለልጁ - ለተማሪው ለአምስት (5) ወይም ከዚያ-በላይ ተከታታይ-የሆኑ ቀናት መቅረት/absent - ያስፈልገዋል፤
- ለተማሪው - የሕክምና ወይም የጥርስ-ህክምና ቀጠሮዎች፤
- በተማሪው ቤተሰብ-ውስጥ/student's immediate family - ውስጥ ሞት-በመከሰቱ፤

---

26 5-E DCMR § 2101.4; 5-A DCMR § 2102.4ን ተመልከቱ።

27 በ[dcps.dc.gov/page/parent-portal](https://dcps.dc.gov/page/parent-portal). ላይ የሚገኝ

28 በ5-A DCMR § 2102.2 ላይ ተመልከቱ።

29 የተማሪዎች፤ ህመማቸው በሆስፒታል ውስጥ መግባት የሚያስፈልግ ከሆነ ወይም ከሦስት (3) ሳምንታት በላይ በቤት ውስጥ ሆነው-ከቆዩ - ለቤት-ውስጥ ወይም ሆስፒታል ውስጥ የትምህርት አሰጣጥ ፕሮግራም (Home and Hospital Instruction Program (HHIP) - ብቁ-ሊሆኑ ይችሉ-ይሆናል። ተጨማሪ-መረጃዎችን ለማግኘት፣ በ[dcps.dc.gov/service/home-and-hospital-instruction](https://dcps.dc.gov/service/home-and-hospital-instruction). ላይ ተመልከቱ።

- መባረር (Exclusion) - ከኮሎምብያ ዲስትሪክ ባለስልጣናት በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት - ባለው ተገልሎ-የመቆየት (quarantine)፣ ተላላፊ-በሽታ፣ ብክለት (infection)፣ ተወርሮ-መበከል (infestation)፣ ወይም ሌላ ከሌሎች ተማሪ በሕክምና ወይም ለጤና ምክንያቶች በሚከሰትበት ሳቢያ፤
- ተማሪው የዳኝነት-ሂደቶች (Judicial proceedings) ወይም የፍርድ-ቤት ትዕዛዝ የሚደረግ እንቅስቃሴን - በድርጊቱ አንዱ አካል በመሆን ወይም መጥሪያ-በማግኘቱ ምክንያት ማከፈል በሚያስፈልገው-ጊዜ፤
- የሃይማኖት ክብረ-በዓላትን በሚከበር ጊዜ፤
- የተማሪውን ወላጅ/አሳዳጊ - ወዲያውኑ ወደ የውትድርና ስራቸው ከመሰማራታቸው በፊት ወይም ከተሰማሩበት ቦታ ሲመለሱ እንዲጎበኙ-ለማድረግ - ተማሪው የሚፈቀድለት - መቅረቶች (Absences)፤
- በትምህርት ቤቱ ርዕሰ-መምህር ወይም በትምህርት ቤቱ ተቀባይነት-ያለው ጠቃላይ-ስራ አስኪያጅ - በተሰጠው ፈቃድ መሠረት፣ ለአስቸኳይ-ጊዜ ሁኔታ ወይም ሌላ የገጠሙ-ሁኔታዎች።

DCPS፤ የሚከተሉትን ተጨማሪ አጋጣሚዎች - እንደ ፈቃድ-ያገኙ መቅረቶች (excused absences) አድርጎ-መድቧል:[30]

- ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍሎች - ተማሪዎች የሚያደርጉት የኮሌጅ ጉብኝት (በትምህርት ዓመቱ-ውስጥ እስከ ሦስት (3) የተጠራቀመ ቀናቶች)፤
- ከK እስከ 8ኛ ክፍሎች ላሉ ተማሪዎች - የትምህርት ቤት ጉብኝቶች (ለምሳሌ፤ የ5ኛ ክፍል ተማሪ፣ ተመዝግቦ-ለመማር ከመወሰን በፊት የመካከለኛ-ደረጃ/middle ትምህርት ቤትን መጎብኘት)። በትምህርት ዓመቱ ውስጥ፣ እስከ አንድ (1) ቀን ያህል - ጥቅም-ላይ ሊውል ይችላል፤
- ለመውለድ-የሚጠበቁ ወይም ወላጅ-የሆኑ ተማሪዎች መቅረቶች - ለተወሰነ የጊዜ-ገደብ በሐኪማቸው በተገለጸው መሠረት መቅረቶች እና ማንኛውም በሕጉ መሰረት መስጠት ያለበት ማመቻቻዎች፤
- ልጆቻችንን ወደ ስራ የመውሰድ-ቀን (Take Our Children to Work Day)፣ እና
- ከሃይማኖራዊ ክብረ-በዓላት ውጪ የሚከበሩ ወይም የሚደረጉ ዝግጅቶች (እስከ አምስት (5) የተጠራቀመ ቀናት - በትምህርት ዓመቱ-ውስጥ)።

የሚከተሉትን መቅረቶች (absences)፤ ከወላጅ/አሳዳጎ የጽሁፍ ሰነድ ሳይቀርብ፣ በትምህርት ቤቱ ማረጋገጫ በተሰጠው መሠረት - ፈቃድ ሊያገኝም የሚችል-ይሆናል:[31]

- በትምህርት ቤት ባለስልጣናቶች፤ ህጋዊ-የሆነ ከትምህርት-ቤት ውጪ እገዳ ወይም ማበረር፤
- በመጥፎ-የአየር ሁኔታ ምክንያት፣ በይፋዊ እንቅስቃሴዎች፣ በክብረ-በዓላት፣ የማይሰሩ-የህንፃ መሣሪያዎች ሲኖሩ፣ ደህንነቱ-ያልተጠበቀ እና ንጽህና-የጎደለው ሁኔታ ሲኖር፣ ወይም ሌላ ሁኔታ(ዎች) ወይም የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች የክፍለ-ጊዜ እገዳዎችን በሚጠይቁ-ጊዜ፤ የትምህርት ክፍለ-ጊዜውን በጊዜያዊነት ማገድ፣ እና
- የኮሎምብያ ዲስትሪክት ባለው ሕጋዊ የመጓጓዣ ለተማሪዎች ማቅረብ ኃላፊነቱን ለመወጣት የማይችልበት፤ የኮሎምብያ ዲስትሪክት መጓጓዣ ለተማሪዎች ማቅረብ ሳይችል-ሲቀር።

ከዚህ-በላይ ከተዘረዘሩት ፈቃድ-ያገኙ መቅረቶች (excused absences) ውስጥ ያልተሸፈኑ - መቅረት እንደሚኖር ተማሪው ወይም ወላጅ/አሳዳጊ ይኖራል-ብለው የሚገምቱ ከሆነ፣ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች ወይም ሌላ ሁኔታዎች - በDCPS ፈቃድ ያገኙትን-ጨምሮ፣ ወይም ከተወሰነ ሁኔታ ወይም ክስተት ጋር ግንኙነት ያለው ቀጣይነት ያለው መቅረት እንደሚከሰት ከጠበቁ፤ ወደ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር - ፈቃድ-ያገኘ መቅረት (excused absence)ን መጠየቂያ ሊያስገቡ-ይችላሉ። ርዕሰ-መምህሩ፣ ውሳኔ ከመወሰኑ-አስቀድሞ፤ ከእርነርሱ - የትምህርት አሰጣጥ ጠቃላይ-ስራ አስኪያጅ ጋር - ፈቃድ ያገኘ የመቅረት (excused absence) ጥያቄውን - ውሳኔውን-ሰጥቶ መፍቀድ-አዳለበትና እንደሌለበት ማማከር አለበት። ማንኛውም መቅረት - ፈቃድ-ያገኘው መቅረት (excused absence)ን መስፈርት-ያላሟላ፣ ወይም ፈቃድ-ያገኘው መቅረት (excused absence)ን ለመደገፍ የሚያስችል አስፈላጊ-የሆኑ ሰነዶችን በተፈቀደው የጊዜ-ገደብ ውስጥ ማቅረብ ካልቻለ፤ መቅረቱ - ፈቃድ-ያላገኘ መቅረት (unexcused absence) ተብሎ ይመደባል።

2. አስፈላጊ-የሆኑ ሰነዶች

ተማሪው፤ **እስከ አራት (4) ተከታታይ ቀናት ያህል ከቀረ**፤ የወላጅ/አሳዳጊ ማስታወሻ - ለመቅረቱ፣ እንደ ሰነድ-ሆኖ በጥቅም-ላይ

30 5-A DCMR § 2102.2(k)
31 በ5-A DCMR § 2102.2. ላይ ተመልከቱ።

ሊውል ይችላል።[32] ማንኛውም እንደዚህ ዓይነት መቅረት - ከላይ በማስታወሻው ላይ እንደምክንያት በተሰጡት ፈቃድ-ያገኘ መቅረት (excused absence) ስር የሚመደብ ከሆነ፤ ፈቃድ-ማግኘት ይችላል።

ተማሪው ለ**አምስት (5) ወይም ከዚያ-በላይ ለሆኑ ተከታታይ ቀናቶች** - ከቀረ፤ በሚከተሉት-መሠረት - ከወላጅ/አሳዳጊ ከቀረበው ከግንኙነቶች ባለፈ ሁኔታ፣ ለመቅረቱ ፈቃድ-እንዲያገኝ ለማድረግ - ተጨማሪ ሰነድ ያስፈልገዋል። የሚከተሉት ሰነዶች - ተቀባይነት ይኖራቸዋል:

- በሕክምና ወይም የጥርስ-ቀጠሮ፤ መቅረቶች (absences): የተማሪውን መቅረት የሚገልጽ፤ ከሐኪሙ ወይም በድርጅቱ ውስጥ ከሚሰራ ሠራተኛ በህጋዊ የቢሮው የራስጌ የደብዳቤ መፃፊያ ወረቀት (letterhead) ባለው ላይ የተፃፈ እና በተገቢው የቢሮው ሹም የተፈረመ የጽሁፍ-መግለጫ መግባት አለበት፤
- የዳኝነት-ሂደቶች (Judicial proceedings): የተማሪውን በዳኝነት-ሂደቶች (judicial proceedings) ላይ መገኘት እንደሚያስፈልገው የሚገልጽ ሰነድ - ከፍርድ-ቤቱ፣ የተማሪውን በሁሉን ተገቢ-በሆኑ ቀናቶች መገኘት-እንዳለበት የሚገልጽ ሰነድ መቅረብ አለበት፤ እና
- በተማሪው የቅርብ-ቤተሰብ ውስጥ፣ ሞት ሲከሰት: የቀብር/Funeral ፕሮግራሞች፤ እንደ ተገቢ-የሆኑ ሰነዶች አቀራረብ ሁኔታ፤ ተቀባይነት ሊኖረው ይችል-ይሆናል።

a. የመለየት (Isolation) እና ተገልሎ-የመቆየት (Quarantine) ሰነዶች

በግለሰቦች ህመም ምክንይት ወይም በሰፊው የሕዝብ ጤና ሁኔታዎች ምክንያት፣ እንደ ተለይቶ-መቆየት ወይም መገለል/quarantine ሆኖ፣ ተማሪዎች በመኖሪያ-ቤት ውስጥ መቆየት-የሚያስፈልጋቸው ጊዜያቶች ሊኖሩ-ይችላሉ። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ጊዜ፣ ወላጅ/አሳዳጊ ትምህርት ቤቱን እና የጤና ክትትል ባለሞያተኞችን ማሳወቅ ያለበት፣ እና ከተገቢው ሰነዶች ጋር - መቅረቱ/absence ፈቃድ-ሊያገኝ ይችላል። ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ከመመለሱ በፊት፣ ማንኛውም ሰነዶች ያስፈልጉ ከሆነ፣ የትምህርት ቤት ሠራተኞች፣ ምን-ዓይነት እንደሆነ መመሪያ-ትዕዛዞችን ይሰጣሉ።

### D. የክትባት/Immunization እና በትምህርት-ገበታ የመገኘት (Attendance) መስፈርቶች

በኮሎምብያ ዲስትሪክት ትምህርት ቤት ውስጥ ለመማር፤ የሕዝብ፣ የግል፣ የቤተክርስቲያን፣ እና ገለልተኛ ትምህርት ቤቶች ውስጥን ጨምሮ ለመማር፤ ተማሪው በዲሲ ጤና (DC Health) መስፈርቶች ውስጥ ተገዢ-መሆንና ክትባት-የወሰደ መሆን አለበት።[33,34] DCPS የክትባት መስፈቶችን አያዘጋጅም፤ ነገር ግን ሁሉም ተማሪዎች ከእነዚህ መስፈርቶች ጋር ተገዢ-እንደሆኑ ማረጋገጥ-አለበት። የዲሲ ሕግ፤ ውሱን-በሆኑ ክስተቶች ስር - የተማሪ የክትባት መስፈርቶችን - በሕክምና ወይም በሃይማኖት ምክንያት እንዲነሳ-ለማድረግ (exemptions)፤ ሊፈቅድ-ይችላል።[35]

የተማሪው የሕክምና መዝገብ - ለሕግ-ተገዢነትን የማያሳይ ከሆነ፤ ወይም በሕክምና ወይም በሃይማኖት-ምክንያት እንዲነሳ-የሚያደርግ (exemptions) በሰነድነት-ከሌለ፤ ትምህርት ቤቱ ወዲያውኑ - ለወላጅ/አሳዳጊ ወይም ለአዋቂ-ተማሪው፤ የክትባት(ቶች) መረጃ እንደሌለ - በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት። ተማሪው በሃያ (20) የትምህርት ቀናት ገደብ ውስጥ - ለሕጉ-ተገዢነቱን ለማሳየት ካላመጣ፤ ወላጅ/አሳዳጊ አስፈላጊ-የሆነውን ሰነድ እስከሚያመጡ ድረስ - ትምህርት ቤቱ፣ ተማሪው ከትምህርት ቤት እንዲወገድ ያደርጋል። ይህ መሰሉ መወገድ/removal - ፈቃድ-ያላገኘ መቅረት ተብሎ ከግምት-ውስጥ የሚገባ እና፣ በSection F ውስጥ በተዘረዘረው መሠረት፣ ጣልቃ-ገብነቶች ሊያስፈሉ-ይችላሉ።

32 DCPS፣ የቀለም-ትምህርት የቀን-መቁጠሪያውን በአራት ተርሞች ይከፍላል፤ ይህም የውጤት-አሰጣጥ ወቅቶች (grading periods) ተብሎ፣ ወይም አድቫይዘሪ ፒሬድስ (advisory periods) ተብሎ-የሚታወቅ ሲሆን፤ እያንዳንዱ እኩል-የሆኑ በሚባል-ቁጥር ባላቸው የትምህርት ቀናትን የያዙ-ናቸው። በአንድ-ሴሚስተር (semester) ውስጥ - ሁለት ተርሞች (terms)፣ አሉ።

33 እባካችሁ፤ የዲሲ ጤና ገጽ/DC Health’s siteን በdchealth.dc.gov/page/immunizations ላይ፣ ስለ ክትባት መረጃ ለማግኘት - ጎብኙ።

34 *D.C. Official Code § 38-503; 5-E DCMR § 5300.1,* et seq. *ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፣ እባካችሁ - የDC Office of the State Superintendent of Education (OSSE)’ን* ‘No Shots, No School!’ን ጎብኙ የኮሎምብያ ዲስትሪክት የክትባት ፖሊሲ (District of Columbia Immunization Policy) ለበአካል-ተገኝቶ በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት (Attendance) ድህረ-ገጹ፣ በ bit.ly/NoShotsNoSchool.

35 ተጨማሪ-መረጃዎችን ለማግኘት፣ እባካችሁ በbit.ly/NoShotsNoSchool ላይ ጎብኙ።

### E. በትምህርት ቤት ስፖንሰር-በሆኑ እንቅስቃሴዎች ምክንያት፤ የሚደረጉ መቅረቶች (Absences)

በትምህርት ቤት ስፖንሰር በተደረገ ወይም - በግዳጅ-መደረግ ባለበት እንቅስቃሴ ምክንያት ከትምህርት ቤት ለቀሩ-ተማሪዎች፤ በእንቅስቃሴው ባህሪይ-መሠረት እንደተገኙ/present ወይም ፈቃድ-ያገኘ ሆኖ - ምልክት-ይደረጋል።

1. አትሌቲክስ (Athletics)

በመደበኛ የትምህርት ሰዓታት ውስጥ በሚካሄዱ በDCPS-ስፖንሰር በተደረገ የአትሌቲክ ዝግጅቶች ላይ ተማሪዎች በሚካፈሉበት-ጊዜ፤ እንደ 'የተገኙ/present' ሆኖ ይወሰድላቸዋል። ተማሪዎች - በሁሉም በትምህርት-ገበታ የመገኘት (attendance) መስፈርቶች፣ በዲሲ ድንጋጌዎች እና በDCPS ፖሊሲ ስር፤ መከተል አለባቸው። በማንኛውም ልምምድ ውስጥ ለመካፈል፣ ማንኛውም አትሌቲክስ ሙከራ፣ ልምምድ፣ ጨዋታ፣ ወይም ውድድር ለመሳተፍ፤ ተማሪው በትምህርት ቀኑ ላይ - ፈቃድ-ያገኘ መቅረት (excused absence) እስከሌለው ድረስ፤ ወደ ትምህርት ቤት ከዝግጅቱ-በፊት መገኘት አለበት።[36]

በህክምና-ሁኔታ ብቁነትን ያገኙ በርቀት (virtual) የትምህርት-አሰጣጥ ውስጥ የሚሳተፉ ተማሪዎች፤ በአካል-ተገኝቶ (in-person) እንቅስቃሴዎች እና አትሌቲክስ ውስጥ ለመሳተፍ ብቁ-አይሆኑም። በተመሣሣይነት፤ ተገልሎ-በመቆየት (quarantine በማድረግ) ምክንያት፤ ተማሪው ከቀረ፤ ለበአካል-ተገኝቶ (in-person) እንቅስቃሴዎች እና አትሌቲክስ ብቁ-መሆን አይችልም።[37]

2. ሌላ በDCPS-ስፖንሰር በተደረጉ እንቅስቃሴዎች

በDCPS-ስፖንሰር በተደረጉ ዝግጅቶች፣ በመስክ-ጉዞዎች ውስጥ የሚሳተፉ፣ ወይም በመደበኛ የትምህርት ቀኑ ወቅት ወደ ውጪ-ሃገር ለትምህርት የተጓዙ ተማሪዎች፤ በትምህርት-ገበታ የተገኙ/present ሆነው-ይወሰዳሉ።

3. የግል የትምህርት ፕሮግራም (Individualized Education Program (IEP) ወይም የ'504 Plan' አገልግሎት - አሰጣጥ

በ'IEPs' ወይም በ'504 plans' ላይ በሰነድነት በተቀመጠው - ተዛማጅ የሆኑ አገልግሎቶችን ለማግኘት ክፍለ-ጊዜው ውስጥ ያልተገኙ ተማሪዎች፤ በትምህርት-ገበታ የተገኙ/present ሆነው-ይወሰዳሉ።

4. እገዳዎች (Suspensions)

በትምህርት ቤት እገዳዎች (suspensions) ውስጥ እያሉ፤ ተማሪዎች - የተገኙ/present - ሆነው-ምልክት ይደረጋል። ከትምህርት ቤት-ውጪ እገዳ (out-of-school suspension) ውስጥ እያሉ፤ ተማሪዎች - ፈቃድ-ያገኘ/excused - ሆነው-ምልክት ይደረጋል።

### F. ከመቅረቶች ጋር ተዛማጅ-የሆነ፤ በትምህርት ቤት መሠረት ያደረገ በትምህርት-ገበታ ላይ የመገኘትና አለመገኘት ጣልቃ-ገብነቶች (School-Based Attendance Interventions)

1. ከK-2 ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ፣ ተማሪዎች

ትምህርት ቤቶች - የሚከተሉትን - በትምህርት ቤት ላይ መሠረት ያደረገ በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘትና-አለመገኘት ጣልቃ-ገብነቶችን (school-based attendance interventions)ን - ከK-12 ክፍሎች ውስጥ ላሉ - የርቀት (virtual) ትምህርት-አሰጣጥን የሚያገኙትን ጨምሮ፤ ለሁሉም ተማሪዎች - ማስፈጸም ያስፈልጋቸዋል:

[36] 5-F DCMR § 104.8.

[37] የ'Title 5-F' - DCMR የሚያስተዳድረው፣ 'interscholastic athletic policies' ለሕዝብ ትምህርት ቤቶች፣ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች እና በዲስትሪክቱ ውስጥ የሚገኙ የግል ትምህርት ቤቶች/independent schools።

| የጊዜ አቀማመጥ | የትምህርት ቤት ኃላፊነቶች/School Responsibilities |
|---|---|
| **እያንዳንዱ ፈቃድ-ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረት/unexcused absence (ሙሉ ወይም በከፊል - መቅረት/absence)** | **ሮቦ-ኮል (Robo-call)** በእያንዳንዱ ምሽት-ላይ ለቤተሰቦች የሚላክ፣ ተማሪው አንድ (1) ፈቃድ-ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረት (unexcused absence) እንዳለው-የተላከ-ነው።<br><br>**ቴክስት መልዕክት (text message)** ወደ ተማሪው ቤተሰብ - በእያንዳንዱ ምሽት ላይ - ከ6 እስከ 12ኛ ክፍል ውስጥ ለሚገኙ-ተማሪዎች - ከአንድ (1) ሙሉ-ቀን ጋር እኩል-የሆነ የተጠራቀመ ፈቃድ-ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ ላይ መቅረት/unexcused absence ያላቸው እና መልዕክቶችን/messagesን ለመላክ - DCPS፣ የወላጅ-ስምምነት ያለው - የተላከ-ነው። |
| **3 የተጠራቀመ (cumulative) - በከፊል ወይም የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences)** | 'AC/AD'፤ ከአስፐን (Aspen) ላይ፤ የ**3-ቀን ዓለም-ዓቀፍ የመቅረት (Universal Absence) ደብዳቤን** ለወላጅ/አሳዳጊ - ይልካል።<br><br>*ለርቀት (virtual) ተማሪዎች ብቻ*፤ 'AC/AD'፣ **የደህንነት-ሁኔታን ማረጋገጫ (wellness check)ን** ለማጠናቀቅ፣ ወደ ተማሪው መኖሪያ-ቤት የስልክ-ጥሪ ያደርጋል። የደህንነት-ሁኔታን ማረጋገጫው (wellness check) ማካተት ያለበት፤ ስለ ተማሪው በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት (attendance) ሁኔታ መወያየት - የቴክኖሎጂ፣ ሌላ እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮች ወይም አስቸጋሪና-ፈጣኝ ሁኔታዎች-ካሉ፣ እና አስፈላጊ የሆኑ የመረጃ-ምንጮች - ለተማሪው-ስኬታማ-መሆን ያስፈልጉ-እንደሆነ ጨምሮ፤ ይወያየሉ። |
| **4 የተጠራቀመ (cumulative) የከፊል ወይም የሙሉ-ቀን መቅረቶች/** absences **(ፈቃድ-ያገኘ ወይም ያላገኘ/excused or unexcused)** | ስለ ተማሪው በትምህርት-ገበታ መገኘትና አለመገኘት (attendance) ሁኔታ ለመወያየት፣ **አስተማሪው ወደ ተማሪው መኖሪያ-ቤት፣ የስልክ-ጥሪ ያደርጋሉ።** |
| **5 የተጠራቀመ (cumulative) - በከፊል ወይም የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences)** | 'AC/AD'ው፤ '**5-Day Universal Absence Letter**' ከአስፐን (Aspen) ላይ ወደ ተማሪው መኖሪያ-ቤት - የተማሪ በትምህርት ገበታ-ላይ የመገኘት ኮንፈረንስ (Student Attendance Conference (SAC) እንደሚካሄድ ለወላጅ/አሳዳጊ ለማሳወቅ ይልካል።[38] |
| **5 የተጠራቀመ (cumulative) የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኙ መቅረቶች/unexcused absences** | 'AC/AD'ው፤ የመቅረቱን ከስር-መሠረት ያለውን ችግር በሰነድነት ለማስቀመጥ እና ለመወሰን፣ እና አስፈላጊ የሆኑ ጣልቃ-ገብነቶችን ለመስጠት እና በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት የእርምጃ ዕቅድ (Attendance Action Plan)ን ለመቅረጽ፤ መምራቱ(referral)-በተደረገ በ5 (አምስት) ቀናቶች ውስጥ፣ **'SAC'ን - ከወላጅ/አሳዳጊ ጋር** እና ከተማሪው ጋር፣ ተገቢ-ከሆን፤ ያካሂዳል። ይህን ስብሰባ - በአስፐን (Aspen) ላይ፣ 'AC/AD'ው በሰነድነት-ያስቀምጣል። ተማሪው - 'IEP' ካለው፤ AC/ADው - የአካባቢውን የትምህርት ድርጅት ወኪል ተጠሪ (local education agency representative designee (LEARD)ን እና ጉዳይ-አስፈፃሚው/case managerን ማሳወቅ አለበት።<br><br>ሣምታዊ-በሆነ አሠራር መሠረት፤ ወደ 5(አምስት)-ቀን ፈቃድ ያላገኘ በትምህርት ገበታ-ላይ ያለመገኘት (unexcused absence) የገደብ-ደረጃ/threshold ላይ የደረሱትን ሁሉንም ተማሪዎች ዝርዝር፤ የ'SAC' ስብሰባ በተደረገ-ጊዜ እንቅፋት-ናቸው ተብለው ማጠቃለያ ከተሰጠው ሪፖርት ጋር አድርጎ - 'AC/AD'ው ለ'MTSS Leadership Team' - ያቀርባል።<br><br>**ወደ አምስት (5)-ቀን ፈቃድ-ያላገኘ መቅረት/unexcused absence የገደብ-ደረጃ/threshold የደረሱ-ተማሪዎች፤ በ'MTSS leadership' ቡድን/team - ሌላ-ተጨማሪ ዒላማ-የተደረገበት እርዳታዎች ያስፈልጋቸው-እንደሆነ ከግምት-ውስጥ ለማስገባት - እንደገና-ምልከታ ይደረጋል።** የ'Tier II' ወይም 'III' መመራት/referral - ለማንኛውም ተማሪ የሚያስፈልግ ከሆነ፤ ይህ መመራት/referral፣ በMTSS system ውስጥ የሚደረግ እና በትምህርት ቤት-መሠረት ያደረገ (school-based) የ'MTSS' ጣልቃ-ገብነት የግንኙነት ሠራተኛው (intervention POC) - 'AC/AD'ውን በማግኘት - በስራ-ውሎ የሚገኘው የ'SAC documents'ን ለማግኘት ያነጋግራሉ።[39] |

38 በ5-A DCMR § 2103.4 ላይ ተመልከቱ።

39 ጉዳተኝነት ሊኖረው ይችላል ተብሎ የሚጠረጠረውን ተማሪ፤ የመጀመሪያ (initial) ግምገማ ለማዘግየት - 'MTSS' ጥቅም-ላይ ሊውል አይችልም። ከጉዳተኝነት ግአር የሚገኝ ልጅ ነው ለተባለ ተማሪ - በሚያስፈልጉት በልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ላይ፤ DCPS ሁልጊዜ፣ የልዩ ትምህርት (special education) መምራት/referralን እና የመጀመሪያ (initial) ግምገማ እንዲደረግ ማነሳሳት አለበት።

| | |
|---|---|
| **7 የተጠራቀመ (cumulative) የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኙ መቅረቶች** | AC/AD፤ **ሜትሮፖሊታን ፖሊስ መምሪያ (Metropolitan Police Department (MPD)** - የማስጠንቀቂያ-ደብዳቤን፣ አስፐን (Aspen) በመጠቀም፤ ለወላጅ/አሳዳጊ ይልካል። |
| **10 የተጠራቀመ (cumulative) - በከፊል ወይም የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences)** | AC/AD፤ ከአስፐን (Aspen) ላይ፤ የ**10-ቀን ዓለም-ዓቀፍ የመቅረት (Universal Absence) ደብዳቤን** ለወላጅ/አሳዳጊ - ይልካል።<br><br>**የ'MTSS leadership' ቡድን/team፤ የሁሉንም ተማሪዎች (ዕድሜያቸው ከ5-17) የሆኑትን፣ የአስር (10)-ቀን ፈቃድ-ያላገኘ መቅረት (unexcused absence) የገደብ-ደረጃ ላይ የደረሱትን ዝርዝሮች የሚመለከት ሲሆን**፣ ተጨማሪ ዒላማ-የተደረገበት እርዳታ ያስፈልግ-እንደሆነ ከግምት-ውስጥ ያስገባሉ። የ'Tier II' ወይም 'III' መመራት/referral - ለማንኛውም ተማሪ የሚያስፈልግ ከሆነ፤ ይህ መመራት/referral፣ በMTSS system ውስጥ የሚደረግ እና በትምህርት ቤት-መሠረት ያደረገ (school-based) የ'MTSS' ጣልቃ-ገብነት የግንኙነት ሠራተኛው (intervention POC) - 'AC/AD'ውን በማግኘት - በስራ-ውስጥ የሚገኘው የ'SAC documents'ን ለማግኘት ያነጋግራሉ። |
| **10 የተጠራቀመ (cumulative) የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኙ መቅረቶች** | ዕድሜአቸው ከ5-13 ለሆኑ ተማሪዎች - ብቻ: ሁሉም በትምህርት ገበታ የመገኘት ጣልቃ-ገብነቶች (attendance interventions) ተፈፃሚ-እንዲሆኑ ከተደረገ እና በሰነድነት በአስፐን (Aspen) ውስጥ ከተቀመጠ፤ 'AC/AD'ው፣ በትምህርታዊ ቸልተኝነት፤ **ተማሪውን ወደ 'CFSA' ይመራዋል።** |
| **15 የተጠራቀመ (cumulative) - በከፊል ወይም የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences)** | AC/AD፤ ከአስፐን (Aspen) ላይ፤ የ**15-ቀን ዓለም-ዓቀፍ የመቅረት (Universal Absence) ደብዳቤን** ለወላጅ/አሳዳጊ - ይልካል። |
| **15 የተጠራቀመ (cumulative) የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኙ መቅረቶች** | ዕድሜአቸው ከ14-17 ለሆኑ ተማሪዎች - ብቻ: ሁሉም-ጣልቃ ገብነቶች ከተሞከሩ እና በአስፐን/Aspen ውስጥ በሰነድነት-ከተያዙ፤ 'AC/AD' ከትምህርት-ገበታ ባለሞያተኛቸው ጋር ጎን-ለጎን በመሆን፣ **ወደ 'Court Social Services Division' እና 'the Office of the Attorney General' - ተማሪ/ቤተሰብን - ይመራል/refer-ያደርጋል።** |
| **20 *ተከታታይ/consecutive* የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኘ መቅረቶች/unexcused absences**[40] | 'AC/AD'ው፤ የ**'initial withdrawal letter'**ን - ለወላጅ/አሳዳጊ ይልክ እና፣ ለወላጅ/አሳዳጊ የተማሪውን ከትምህርት ቤት ለመውጣት-ብቁነቱን ለማሳወቅ፤ **ወደ ተማሪው መኖሪያ ቤት የስልክ-ጥሪ** ያደርጋል።<br><br>'AC/AD'ው፤ የወላጅ/አሳዳጊን ለመልቀቅ (withdraw ለማድረግ) ያለውን-ፍላጎት ለማሳወቅም፤ ሁሉንም የማግኛ-ጥረቶችን ካጠናቀቀ በኋላ፤ የ**'final withdrawal letter'**ን - ለወላጅ/አሳዳጊ መላክም አለበት። ትምህርት ቤቶች፤ ተማሪውን እንዲወጣ ከማድረጉ (withdrawing a student) በፊት፤ ሁሉንም አስፈላጊ የሆኑትን የጣልቃ-ገብነቶች እርምጃዎች ማከናወን *አለበት*፤ እና ትምህርት ቤቶች - ሁሉንም ሰነዶች በአስፐን (Aspen) ላይ መመዝገብ ያለባቸው እና፣ ከርዕሰ-መምህሩ እና የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጁ ማጽደቂያ-ፈቃድ ማግኘት አለባቸው። በልዩ ትምህርት አገልግሎቶች አማካኝነት 'IEP' የሚያገኙ ተማሪዎች፤ ትምህርት ቤቱ ወላጅን ለማግኘት ተጨማሪ ተገቢ-የሆኑ ወላጅን/አሳዳጊን-የማነጋገር ጥረቶችን - እንዳደረገ ሳያሳይ - ሊለቀቁ (withdrawn ሊደረጉ) የማይችሉ እና፣ ከDCPS የልዩ ትምህርት-አሰጣጥ (DCPS Division of Specialized Instruction) ፈቃድ-ሳያገኝ መልቀቅ-አይችሉም። |

2. በPre-K ውስጥ የሚገኙ፣ ተማሪዎች

የPre-K ተማሪዎች፤ ስለ ፈቃድ-ያላገኘ እና ፈቃድ ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረቶች - ልክ እንደ ከK-12ኛ ክፍል-ተማሪዎች ሁሉ በአንድ-ዓይነት በሆነ ሁኔታ ላሉት መስፈርቶች ተገዢ-ይሆናሉ። ምንም-እንኳን - ወደ 'CFSA'፣ በትምህርት-ገበታ ላይ በመገኘትና-ባለመገኘት ላይ መሠረት ያደረገ መምራት - (attendance-based referrals) - ዕድሜያቸው ከአምስት (5) ዓመት-በታች ለሆኑ ተማሪዎች ባያስፈልግም፤[41] ትምህርት ቤቶች፣ በትምህርት ቤት ላይ መሠረት ያደረገ በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘትና-አለመገኘት ጣልቃ-ገብነቶችን (school-based attendance interventions)፣ ከዚህ-በታች በተገለጸው መሠረት - ያስፈጽማሉ:

40 D.C. Official Code § 38-236.04(c)ን ተመልከቱ።

41 የPre-K ተማሪዎች - በትምህርት ቤት የመገኛ አስገዳጅ-የሆነ እድሜ ባለመሆኑ ምክንያት፤ የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences)ን - 'CFSA'ን በማነጋገር፣ ትምህርት ቤቶች ሪፖርት ማድረግ አይችሉም።

| የጊዜ አቀማመጥ (Timeline) | የትምህርት ቤት ኃላፊነቶች/School Responsibilities |
|---|---|
| **እያንዳንዱ ፈቃድ-ያላገኘ (Each unexcused) በከፊል ወይም የሙሉ-ቀን መቅረቶች (absences)** | **ሮቦ-ኮል (Robo-call)** በእያንዳንዱ ምሽት-ላይ ለቤተሰቦች የሚላክ፣ ተማሪው አንድ (1) ፈቃድ-ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረት (unexcused absence) እንዳለው-የተላከ-ነው። |
| **3 የተጠራቀመ (cumulative) - በከፊል ወይም የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences)** | AC/AD፤ ከአስፐን (Aspen) ላይ፤ የ**3-ቀን ዓለም-ዓቀፍ የመቅረት (Universal Absence) ደብዳቤን** ለወላጅ/አሳዳጊ - ይልካል። |
| **4 የተጠራቀመ (cumulative) የከፊል ወይም የሙሉ-ቀን መቅረቶች/**absences **(ፈቃድ-ያገኘ ወይም ያላገኘ/excused or unexcused)** | ስለ ተማሪው በትምህርት-ገበታ መገኘትና አለመገኘት (attendance) ሁኔታ ለመወያየት፣ **አስተማሪዎች ወደ ተማሪው መኖሪያ-ቤት፣ የስልክ-ጥሪ ያደርጋሉ።** |
| **5 የተጠራቀመ (cumulative) - በከፊል ወይም የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences)** | 'AC/AD'ው፤ '**5-Day Universal Absence Letter**' ከአስፐን (Aspen) ላይ ወደ ተማሪው መኖሪያ-ቤት - 'SAC' እንደሚካሄድ፣ ለወላጅ/አሳዳጊ ለማሳወቅ ይልካል። |
| **5 የተጠራቀመ (cumulative) የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኙ መቅረቶች** | AC/ADው፤ የመቅረቱን ከስር-መሠረት ያለውን ችግር በሰነድነት ለማስቀመጥ እና ለመወሰን፣ አስፈላጊ የሆኑ ጣልቃ-ገብነቶችን ለመስጠት እና በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት የእርምጃ ዕቅድ (Attendance Action Plan)ን ለመቅረጽ፤ **'SAC'ን ከወላጅ/አሳዳጊ ጋር** ያካሂዳል። ይህን ስብሰባ - በአስፐን (Aspen) ላይ፣ 'AC/AD'ው በሰነድነት-ያስቀምጣል። የ'Early Childhood Education (ECE) Family Service' የእርዳታ ቡድን (Title 1 schools)ን - ለሚያገኙ ትምህርት ቤቶች፤ ወደ 'ECE Family Services' ቡድኑ፤ መምራት (referral) - መደረግ-አለበት።<br><br>'AC/AD' - ቤተሰቡን - በስልክ-ጥሪዎች፣ በቴክስቶች (texts)፣ እና በኢሜሎች ማግኘት ካልቻለ፤ በአስቸኳይ-ጊዜ ተጠሪ የሆነውን አድራሻዎች እና ሌሎች የሚታወቁ አድራሻዎችን ማነጋገር አለባቸው። ምንም ዓይነት ግንኙነት ማድረግ ካልተቻለ ወይም የተማሪውን ጤናማና ደህንነት ለማረጋገጥ ካልተቻለ፤ ቡድኑ፣ ከ'ECE' ቡድን ጋር መማከር እና ለ'CFSA' መምራት (referral) ማድረግ ማስፈለግና አለማስፈለጉን መወያየት-አለበት። |
| **10 የተጠራቀመ (cumulative) የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኙ መቅረቶች** | 'AC/AD'ው፤ **'10-Day Universal Absence Letter**' ከአስፐን (Aspen) ላይ ወደ ተማሪው መኖሪያ-ቤት ይልካል።<br><br>ዕድሜአቸው ከ5-13 ለሆኑ ተማሪዎች - ብቻ: ሁሉም በትምህርት ገበታ የመገኘት ጣልቃ-ገብነቶች (attendance interventions) ተፈፃሚ-እንዲሆኑ ከተደረገ እና በሰነድነት በአስፐን (Aspen) ውስጥ ከተቀመጠ፤ 'AC/AD'ው፣ በትምህርታዊ ቸልተኝነት፤ **ተማሪውን ወደ 'CFSA' ይመራዋል።** |
| **20 የተጠራቀመ (cumulative) የሙሉ-ቀን ፈቃድ-ያላገኙ መቅረቶች/unexcused absences**[42] | 'AC/AD'ው፤ የ**'ደህንነት-ሁኔታን ማረጋገጫ/wellness check'**ን በስልክ-ጥሪዎች፣ በቴክስቶች (texts) እና ኢሜሎች አማካኝነት ለማጠናቀቅ፤ የተማሪውን ቤተሰብ ያነጋግራል። የደህንነት-ሁኔታን ማረጋገጫው (wellness check) የሚያካትተው፤ ስለ ተማሪው በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት (attendance) ሁኔታ መወያየት - በቴክኖሎጂ ላይ እንቅፋት-የሆኑ ነገሮችን፣ ሌላ አስቸጋሪና-ፈታኝ ሁኔታዎችን ካሉ-መለየትን እና አስፈላጊ የሆኑ የመረጃ-ምንጮች ለተማሪው-ስኬታማ-መሆን ያስፈልጉ-እንደሆነና-እንዳልሆነ - ጨምሮ፣ ውይይቶችን ያካትታል።<br><br>'AC/AD'ው፤ የአስቸኳይ-ጊዜ ተጠሪዎችን እና ሌሎች የታወቁ በመገኛ-ዝርዝር ውስጥ የሚገኙትን ያነጋግሯሉ፤ እና ከ'Central Services Attendance' ባለሞያተኛ ጋር እና ከ'ECE' ክፍክ/Division' ጋር፤ **የመልቀቅ ውሳኔ (withdrawal determination)**ን ከመወሰን-አስቀድሞ ማማከር ያስፈልገዋል።<br><br>ከ'Pre-K' ተማሪዎች፤ ፈቃድ-ባላገኙ መቅረቶች/unexcused absences ምክንያት - ያልተመዘገቡ-ሊሆኑ የሚችሉ፤ ነገር-ግን አስፈላጊ-የሆነ አይደለም። |

[42] D.C. Official Code § 38-236.04(c)ን ተመልከቱ።

| | |
|---|---|
| | የPre-K ተማሪዎች ሊያደርጉ የሚችሉት፤ ነገር ግን በመስፈርትነት የተቀመጠላቸው ያልሆነው፤ ተማሪው 20 የሙሉ የትምህርት-ቀን ተከታታይ የሆነ ፈቃድ ያላገኘ መቅረቶች (unexcused absences) ከሌለው በስተቀረ፤  ገብቶ-እንዳይማር ሊደረግ የማይችል እና ትምህርት ቤቱ የሚከተሉትን ማድረግ አለበት:<br>• ሁሉንም ቤተሰብን ለማግኘት የተደረጉ ጥረቶችን እና የተሰጡትን የእርዳታ አገልግሎቶች በሰነድነት-መያዝ፤<br>• ከሁሉም የልዩ ትምህርት (special education) ማስታወቂያ መስፈርቶች ጋር፣ ተገዢ-መሆን፤ እና<br>• ከማዕከላዊ አገልግሎቶች/Central Services ECE ክፍል/Division - ማጽደቂያ/approval ያገኙ ማንም ከPre-K ተማሪ የሆነ፤ ዘግይቶ ወደ ትምህርት ቤት በመድረስ ምክንያት፤ ገብቶ-እንዳይማር ሊደረግ አይችልም። |

### G. በተደጋጋሚ-ከመቅረት (Absenteeism) ጋር ተዛማጅ-የሆኑ፣ የተከለከሉ እርምጃዎች

በዲሲ ውስጥ የሚገኝ-ማንም ተማሪ፣ በትምህርት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ እንዲለቅ (withdrawn) እንዲያደርግ የሚደረግበት ነገር አይኖርም፤ ይልቁኑ-ይህ ሊሆን የሚችለው ቢያንድ በአንድ (1) ቀን - በመጀመሪያ የትምህርት ሦስት(3) ሣምንታት ውስጥ ማስታወቂያ-ሳይሰጥ - እንደ መቅረት (absence) ወይም ወደ ሌላ የትምህርት ተቋም መዛወሩን ያሉ ማስታወቂያዎችን ሳይገልጽ፤ በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት ካልቻለ-ነው። ትምህርት ቤቶች፤ "ካለምንም-ምክንያት አለመምጣት/no show" ፕሮቶኮሎችን፤ ማንኛውም ተማሪ እንዲለቅ-ከማድረግ (withdrawing) በፊት ማሟላት አለባቸው። "ካለምንም-ምክንያት አለመምጣት/no show ፕሮቶኮሎች"፤ ሂደቱ ሊከናወን የሚችለው፣ ተማሪዎች በሚማሩበት ጊዜ ከትምህርት ቤት እንዲልቅቁ (withdrawn) በሚደረጉ ጊዜ ሲሆን፣ የተመዘገቡ ከሆነ፣ ነገር ግን ተገኝተው-በማይማሩበት ጊዜ የሚከናወን ይሆናል።

ተማሪው የተጠራቀመ ከ20 ወይም ከዚያ-በላይ *ተከታታይ* የሙሉ-የትምህርት-ቀን ፈቃድ-ያላገኘ ከትምህርት-ገበታ መቅረቶች (unexcused absences) ከሌለው በስተቀረ፤ እና ትምህርት ቤቱ ሁሉንም የሚፈለጉትን እርምጃዎች መውሰዱን እና የተማሪዎችን ቤተሰብ ማነጋገሩን - በሰነድነት ካልያዘ በስተቀር፤ በተደጋጋሚ በመቀረት (absenteeism) ምክንያት - ተማሪዎች ገብተው-እንዳይማሩ ሊደረግ-አይችልም።[43]

ከክልል-ወሰን ውጪ (out-of-boundary) ውስጥ የሚማሩትን ተማሪዎች ጨምሮ - በተደጋጋሚ-በመቅረት (absenteeism) - ተማሪዎች፣ ከትምህርት ቤታቸው እንዲዘዋወሩ መደረግ-የለባቸውም።[44] Students may only beተማሪዎች የማይማሩ-የሚድረገው (unenrolled የሚሆኑት)፣ ከሃያ (20) ወይም ከዚያ-በላይ *የተጠራቀመ/consecutive* የሙሉ-የትምህርት-ቀን ፈቃድ-ያላገኘ መቅረቶች/unexcused absences ካሏቸው-ብቻ ነው።[45]

ያለምክንያት መቅረት ወይም ዘግይቶ ወደ ትምህርት ቤት በመድረስ-ምክንያት - ተማሪዎች ሊባረሩ/expelled ወይም ከትምህርት ቤት ውጭ መታገድ (out-of-school suspension) ወይም በዲሲፕሊን-ምክንያት ያለመመዝገብ (disciplinary unenrollment) ሊዳረጉ ኣይችሉም፤ በትምህርት ቤት ውስጥ ያሉት ከ18-ዓመት በላይ የሆኑበት - ተማሪዎች፣ ከ18 ዓመት በላይ የሆናቸው ተማሪዎች - ከግማሽ-በላይ የሚሆኑት ካልሆኑ በስተቀር።[46]

### H. ለሁለተኛ-ደረጃ ተማሪዎች፤ አርፍዶ መድረስ (Late Arrival)

ተማሪዎች እንደ አርፋጅ (tardy) ሆነው-የሚመዘገቡት - ይፋ-ሆኖ ክፍለ-ጊዜን ከመጀመሪያ ጊዜ በኋላ - ወደ መማሪያ-ክፍላቸው አምስት (5) ደቂቃዎችን ወይም ከዚያ በላይ አርፍደው-ከደረሱ ነው። አርፍደው-ወደ ክፍል የገቡ ተማሪዎች፤ ከቀሪው-ክፍል ጋር የሚሰሩትን ላይ ደረው - ከሌሎቹ እኩል-ሆነው እንዲሰሩ ግልጽ-የሆነ መመሪያ፣ ሊሰጣቸው ይገባል። ተማሪዎች፤ ሁልጊዜ ስራቸውን የማካካሻ (make-up ማድረግ) የሚችሉ-ይሆናል።

በምንም-ጊዜ ቢሆን ተማሪዎች ከኮርሱ የጊዜ-ሰሌዳ በኋላ ቢደርሱም፤ ወደክፍላቸው ገብተው እንዲማሩ መፈቀድ-አለበት። በክፍል-ውስጥ ያለ-ማንኛውም አርፋጅነት (tardy) - ወደ መቅረት (absence) ሊቀየር-የሚችልበት ምንም-አይነት ደረጃ-አይኖረውም። ተማሪው አርፍዶ-ከደረሰ እና የክፍሉን ከፊል-ጊዜ ብቻ ከተካፈለ፤ የተገኙ (present) የሚሆኑ እና አርፋጅ (tardy) ሆነው-ይመዘገባሉ። በርካታ-ተማሪው እንዲያረፍድ ያደረጉት ሁኔታዎች፤ እንደ መቅረት (absence) በአንድ-ላይ ተዳምረው አይቆጠሩም። ለተማሪው አርፋጅነት የሚሰጡ ምላሾች፤ ተገቢ እና ጥሩ-ምክንያት ያላቸው መሆን አለባቸው። ተማሪው፤ በአርፋጅነቱ - ከትምህርት ቤት ሊታገድ (suspend-ሊደረግ) አይችልም።

---

43 D.C. Official Code § 38-236.04(c).
44 D.C. Official Code § 38-236.04(c).
45 D.C. Official Code § 38-236.04(c)ን ተመልከቱ
46 D.C. Official Code § 38-236.04(c). የ'The Student Fair Access to School Amendment Act of 2018'፣ እንደሚተረጉመው ከሆነ የ"ዲሲፕሊን በትምህርት ቤት-ገብቶ አለመማር (disciplinary unenrollment)" እንደ መባረር (expulsion) ወይም ከለፍላጎት ከትምህርት ቤት ተማሪዎ መዛወር፤ አድርጎ ይተረጉመዋል። (D.C. Official Code § 38-236.01(3))

አስተማሪዎች - በእያንዳንዱ የክፍል ማለቂያ-ላይ ተማሪዎች መኖራቸውን ምልከታ ማድረግ-አለባቸው፤ ይህ የሚሆነው አርፍደው-የመጡ ተማሪዎች እንደ-አርፋጅ እንጂ እንደቀሩ-ተደርጎ እንዳይመዘገብ ነው።

### I. ለሁሉም-ተማሪዎች፤ ቀደም-ብሎ መለቀቅ (Early Dismissal)

ለተማሪዎች የቀለም-ትምህርት እና ስሜታዊ ዕድገት - በትምህርት ቤት ውስጥ የመገኘትን ጠቀሜታ ከግምት-ውስጥ በማስገባት፤ ቀደም-ብሎ ለመለቀቅ/early dismissalን - ይህ-ቀደም ብሎ መለቀቅ ከፈቃድ-ያገኘ መቅረት (excused absence) የተያያዘ-ካልሆነ በስተቀረ፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች - ተማሪዎቻቸውን ከትምህርት ቤት ማውጣትን - DCPS አጥብቆ-የማያበረታታው ነገር ነው። ቀደም-ብሎ መለቀቅ (early dismissal) በሚያስፈልግ-ጊዜ፤ ወላጆች/አሳዳጊዎች - ትምህርት ቤቱን ማሳወቅ አለባቸው።

### J. የደረጃ-አሰጣጥ እና ወደሌላ ክፍል መዘዋወር/Grading and Promotion

የሁለተኛ-ደረጃ ተማሪዎች የደረጃ-አሰጣጥ/Grading - ፈቃድ-ባላገኙ መቅረቶች (unexcused absences) መጠራቀም - ተጽዕኖ ሊደርስበት-ይችላል። ተጨማሪ-መረጃዎችን ለማግኘት፣ በ'DCPS *Secondary Grading and Reporting Policy*' ላይ እባካችሁ ተመልከቱ።[47]

ከPre-K እስከ 8ኛ ክፍል-ድረስ ለሚገኙ ተማሪዎች፣ ወደሌላ-ክፍል የመሸጋገር/Promotion እና የመድገም/retention ውሳኔዎች፤ የተማሪውን የውጤት-ሁኔታዎች፣ የቀለም-ትምህርት እድገት፣ እና በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት/attendanceን - ከግምት-ውስጥ ያስገባል። ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፣ እባካችሁ - የ'DCPS *Student Promotion Policy*'ን[48] እና ተዛማጅ-የሆነ መማሪያ/related guidanceን ተመልከቱ።[49]

### K. በትምህርት-ገበታ ላይ የመገኘት መዝገብ (Attendance Record)ን ማስተካከል

1. በትምህርት-ገበታ ላይ የመገኘት መዝገብ (Attendance Record)ን ለማስተካከል-መጠየቅ

ትክክል-ያልሆነ፣ አሳሳች ወይም የተማሪውን ግላዊነት (student's privacy) የሚጥስ-ነው ተብሎ የሚታመነውን - የተማሪ በትምህርት-ገበታ-ላይ መገኘትና-አለመገኘት (student's attendance) መዝገቦችን ጨምሮ ያሉትን ትምህርታዊ መዝገቦች፤ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ተማሪው፤ እንዲስተካከል የመጠየቅ መብት አላቸው። በትምህርት ገበታ ላይ የመገኘት (Attendance) መዝገብን ለማስተካከል የመጀመሪያ-የሆነው ጥያቄ፤ ወደ ትምህርት ቤት ርዕሰ-መምህር - በጽሁፍ መቅረብ ያለበት እና በጥያቄ-ላይ ያለውን በትምህርት-ገበታ ላይ የመገኘት መዝገብ(ቦች)ን መግለጽ እና ሁሉንም ተዛማጅ-የሆኑ ሰነዶችን ማካተት-አለበት።

በጥያቄ ላይ ያለው መቅረቱ(ቶቹ) ለምን መቀየር እንዳለበት የማሳየት ሸክም-ያለው በጠያቂው-ላይ ሲሆን፣ እና ጥብቅ-የሆኑ የማስረጃ ህጎች ተግባራዊ-አይሆኑም። መቅረቱ/absence - ሊለወጥ የሚችለው፣ በሚከተለው-ሁኔታ ብቻ ነው:

- የተወሰኑት መቅረቱ(ቶቹ)/absence(s) - በስህተት የገቡ በመሆናቸው (ለምሳሌ፤ ተማሪው ከትምህርት-ቤት ያረፈደ የነበረ፣ ግን ቀሪ-ተብሎ ተመዝግቧል)፣ ወይም
- ባለማወቅ - ተማሪው፣ የተገኘ/present፣ የቀረ/absent፣ ወይም ያረፈደ/tardy ተብሎ-ተመዝግቦ የነበረ እና ለውጡ እንዲደረግ የሚደግፍ ማስረጃ አለ።

ርዕሰ-መምህሩ፤ ጥያቄዎን የሚመለከት እና ጥያቄውን በተቀበለ  በአስር (10) የትምህርት ቀናቶች ውስጥ - በጽሁፍ ውሳኔውን ለጠያቂው-ያቀባሉ። ርዕሰ-መምህሩ፤ መዝገቡ መስተካከል አለበት ብለው ከወሰኑ፤ ጠያቂው በጽሁፍ እንዲያውቀው የሚድረግ እና ወዲያውኑ ማስተካከያው የሚደረግ ይሆናል። ርዕሰ-መምህሩ፤ መዝገቡ መስተካከል የለበትም ብለው ከወሰኑ፤ ጠያቂው ስለውሳኔው በጽሁፍ እንዲያውቀው የሚድረግ እና ከዚህ-በታች በተገለጸው መሠረት፣ በቅሬታ-አቤቱታ/grievance አማካኝነት-  ለተሰጠው ውሳኔ ይግባኝ-የማለት መብታቸው ይገለጽላቸዋል።

---

47 በ dcps.dc.gov/publication/secondary-grading-and-reporting-policy. ላይ የሚገኝ
48 በdcps.dc.gov/publication/secondary-grading-and-reporting-policy. ላይ የሚገኝ
49 ለDCPS ሠራተኞች- በ SharePoint: ላይ፣ መገኘት-የሚችል Promotion and Retention.

2. የትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት መዝገብ (Attendance Record)ን ለማስተካከል፣ የቅሬታ-አቤቱታ ማቅረቢያን ፋይል-ማድረግ

ወላጅ/አሳዳጊ ወይም አዋቂ-የሆነው ተማሪ (adult student)፤ የትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት መዝገብ (Attendance Record)ን ለማስተካከል፤ ለDCPS ሁሉን-አቀፍ አማራጭ መፍትሄ እና ፍህታዊ-እኩለነት/Comprehensive Alternative Resolution & Equity (CARE) ቡድን፣ በdcps.dc.gov/page/grievance-form የርዕሰ-መምህሩን ውሳኔ በተቀበሉበት በአስር (10) የትምህርት ቀናት ውስጥ፤ በርዕሰ-መምሁሩን ውሳኔ ላይ የቅሬታ-አቤቱታ ማቅረቢያን ፋይል ሊያደርጉ-ይችላሉ።

የ'CARE' ቡድኑ፣ በቀረበው የቅሬታ-አቤቱታ/grievance[50] ላይ ምርመራ-የሚያደርግ እና፣ የመጨረሻ-የምርመራ ውጤቱን የያዘውን የመፍትሄ-መስጫ ደብዳቤን - የቅሬታ-አቤቱታውን በተቀበለበት በሰላሣ (30) የቀን-መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ - ያቀርባል። የቅሬታ-አቤቱታ ውጤቱ፤ በምርመራው-ወቅት ላይ በታየው ማስረጃ-ላይ ብቸኛ-ሆኖ መሠረት ያደረገ ነው።

የ'CARE' ቡድኑ - መዝገቡ(the record) መስተካከል-እንዳለበት ከወሰነ፣ ማስተካከያው በDCPS ይከናወናል። የ'CARE' ቡድኑ - መዝገቡ(the record) መስተካከል-እንደሌለበት ከወሰነ፣ በመፍትሄ-መስጫ ደብዳቤው ውስጥ - ስለተወሰደው ውሳኔ፣ ለወላጅ/አሳዳጊ ወይም አዋቂ-ለሆነው ተማሪ - ያሳውቃሉ። በቅሬታ-አቤቱታ/grievance ሂደት-ላይ ተጨማሪ ዝርዝሮችን ለማግኘት፣ እባካችሁ በdcps.dc.gov/page/studentparentvisitor-grievance-process ላይ ተመልከቱ።

## V. ፖሊሲውን ለማስፈጸም የሚፈለጉ መስፈርቶች

ሁሉም የDCPS ተቀጣሪ-ሠራተኞች፤ በዚህ በተቀረጸው ፖሊሲ መስፈርቶች መገዛት ያስፈልጋቸዋል። አፈፃጸሙን ለመደገፍ፣ የሚፈለጉትን እርምጃዎች እና የጊዜ-አቀማመጥን በዓመታዊ አሰራሩ መሠረት፤ ሁሉም ሠራተኞች እንዲያውቁት ማድረግ፣ ከርዕሰ መምህራኖች ይጠበቅባቸዋል። የዚህ ፖሊሲ አፈፃፀም፤ በመደበኛ የመረጃ ስብስብ (data) ምልከታዎች፣ የመዝገብ ናሙናዎች፣ ከስር ያሉ ሰነዶች ላይ ምልከታ በማድረግ፣ እና ቦታዎችን መጎብኘት -እንደ አስፈላጊነቱ-፤ እነዚህን ሁሉ ያካተተውን፣ በማዕከላዊ የበላይ ክትትል ሂደት አማካኝነት ተጠናክሮ ይካሄዳል።

አስተማሪዎች፤ በየቀኑ በትምህርት-ገበታ መገኘት/attendanceን ማስገባት እና፣ በትምህርት-ገበታ መገኘትና-አለመገኘት ላይ ያሉትን ስህተቶች (attendance errors) የማረም ኃላፊነት-አለባቸው። በትምህርት ቤት መሠረት-ያደረገ የትምህርት-ገበታ መገኘና-አለመገኘት ሠራተኞች (attendance POCs)፤ የትምህርት-ገበታ የመረጃ-ስብስብ (attendance data) በትክክል ስለመግባቱ እና ጊዜውን-በጠበቀ ሁኔታ እንደየአስፈላጊነቱ በአስፐን/Aspen ታርሞ-መግባቱን - ለማረጋገጥ ሃላፊዎች ናቸው። የትምህርት ቤት ርዕሰ-መምህራኖች፤ የትምህርት ቤት ደረጃን የጠበቀ በትምህት-ገበታ መገኘት ትክክለኛነቱን - የመጨረሻ-ማረጋገጫ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው።

ለጥያቄዎች፣ ስልጠና፣ ወይም ማስፈጸምን በተመልከተ - ቁልፍ-የሆነ መመሪያን እና እርዳታን ለማግኘት፤ እባካችሁ የትምህርት ቤታችሁን - በትምህርት-ገበታ መገኘት ሠራተኛ (attendance POC)ን አነጋግሩ።

DCPS፤ እያንዳንዱን ተማሪ፤ በፍህታዊነት፣ የላቀ-በላጭነት ባለው አሰራር፣ በግልጽነት፣ እና ተጠያቂነት ባለው-ሁኔታ ለማገልገል - ቁርጠኝነቱን-ያሳያል። ስለዚህ ፖሊሲ፣ ለማንኛውም ስጋቶች ወይም ጥሰቶችን ሪፖርት-ለማድረግ፤ የሃቀኝነት ቢሮ (Office of Integrity)ን - የኦንላይን-መምሪያ (Online Referral) ቅጽን46 በመሙላት ወይም ወደdcps.cio@k12.dc.gov. ኢሜል በመላክ-ማነጋገር።

---

50 34 C.F.R. §§ 99.20 – .22.

## አባሪ (Appendix) A: ለሁለተኛ-ደረጃ ተማሪዎች፣ የርቀት (Virtual) የትምህርት አሰጣጥ

DCPS፤ ውሱን-ቁጥር ላላቸው የሁለተኛ-ደረጃ ተማሪዎች፣ በተመረጠ የDCPS ኦፖርቹኒቲ አካዳሚስ/Opportunity Academies አማካኝነት፣ የርቀት/virtual የትምህርት-አሰጣጥ ሊሰጥ-ይችላል።[51] ስለዚህ ውሱን-ስለሆነ የርቀት አማራጭ/virtual option፤ የብቁነት መስፈርቶችን ጨምሮ - ተጨማሪ-መረጃዎችን፤ በdcps.dc.gov/page/opportunityacademy ላይ መገኘት-ይችላል።

የርቀት የትምህርት-አሰጣጥ (virtual instruction)ን የሚያገኙ ተማሪዎች፤ በየቀኑ-በትምህርት ገበታ ተገኝተው መማር - በመደበኛ ወይም መደበኛ-ባልሆነ የትምህርት አሰጣጥ (synchronous or asynchronous) ከተመደበላቸው-አስተማሪዎች ጋር በመሆን፣ በተመደበው የኮርስ የጊዜ-ሰሌዳዎች መሠረት መማር-ያስፈልጋቸዋል።

### A. የተማሪን በትምህርት-ገበታ መገኘትና አለመገኘት (Attendance)ን መመዝገብ

መደበኛ-በሆነ (synchronous) የርቀት/virtual የትምህርት-አሰጣጥ ውስጥ የሚካፈሉ ተማሪዎች፤ በስም-ዝርዝር አጠራር ወቅት ላይ - “መገኘት/presence”ን ለማረጋገጥ፣ ካሜራቸው/camerasን እንዲያበሩ ይጠየቃሉ።[52] To support ፍህታዊ-እኩልነት/equityን እና ግላዊነት/privacyን ለመደገፍ፣ የጀርባ-እይታውን ብዥ-እንዲል (blur ለማድረግ) ወይም አማራጭ-የሆነ ከጀርባ-እይታውን ለመቀየር እንዴት-እንደሚችሉ፣ ግልጽ-የሆነ መመሪያ ሊሰጣቸው-ይገባል።

ተማሪው - መደበኛ-በሆነ መንገድ የሚሰጠውን የትምህርት አሰጣጥ (synchronous instruction)ን ሙሉ-ለሙሉ ወይም በከፊል የሆነው የትምህርት-ቀን ውስጥ እንዳይካፈል የሚከለክለው - የቴክኖሎጂ ወይም የኢንተርኔት ማገናኛ ችግሮች ካሉት፤ ተማሪው ወይም ወላጆቹ/አሳዳጊዎቹ ወዲያውኑ ወደ ትምህርት ቤታቸው መደወል እና ችግሩን ሪፖርት ማድረግ እና፤ በዚያን ዕለት የተማሪውን የጊዜ-ሰሌዳውን እንዴት ማስተካከል-እንደሚቻል ትዕዛዝን-መቀበል - አለባቸው። የ‘AC/AD’ው፣ “የአስቸኳይ-ጊዜ (Emergency/ሌላ ፈቃድ-ያገኘ (Other Approved)” ኮድ (code)ን ለማንኛውም በዚህ ምክንያት የተማሪው የሚያመልጠውን ክፍሎች፤ የሚያስገባ-ይሆናል። ተማሪዎች የርቀት (virtual) የትምህርት-አሰጣጡን ከማግኘት የሚከለክሏቸውን ማንኛውንም የቴክኖሎጂ ችግሮች ለመፍታት፤ ትምህርት ቤቱ ወዲያውኑ ከቤተሰቦች ጋር መስራት አለበት።

መደበኛ-ባልሆነ የርቀት የትምህርት-አሰጣጥ (asynchronous virtual instruction) ውስጥ የሚሳተፉ ተማሪዎች፤ በሞጁሉ/module ወቅት - በትምህርት-ገበታ መገኘታቸውን ምልክት-ለማድረግ፣ የስራ-ውጤታቸውን ማጠናቀቅ-ያፈልጋቸዋል።[53]

### B. ከትምህርት ቤት አለመገኘት (Absences)

ለርቀት (virtual) ተማሪዎች፤ የመቅረት-ሁኔታዎች (Absences) - በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት የግንኙነት-ክፍል ሠራተኛው (attendance POC) አማካኝነት ምልከታ-የሚደረግለት እና፣ እንደ “excused” ወይም “unexcused” በሚል-በዚህ ፖሊሲ ላይ ባለው Section C መሠረት ኮድ (code) የሚሰጡት-ይሆናል። ሆኖም-ግን፤ ቤተሰቡ - በቴክኖሎጂ በሚያጋጥሙት አስቸጋሪ-ሁኔታዎች፣ በኤሌክትሮኒክ-ሰነዶችን ማስገባት ካልቻለ፤ የትምህርት ቤት በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት የግንኙነት-ክፍል ሠራተኛ (attendance POC)ን በማነጋገር፣ የሰነዶቹን ሁኔታ ለመግለጽ እና ወደ ትምህርት ቤቱ የሚገቡትን ሰነዶች ቅጂ - አስፈላጊ-ሲሆን፣ ታትሞ (hard copy) እንዲያቀርቡ ማነጋገር አለባቸው።

### C. በትምህርት-ገበታ ላይ ያለመገኘት ጣልቃ-ገብነቶች/Attendance Interventions

በተጨማሪም፣ በትምህርት ገበታ ላይ ያለመገኘት ጣልቃ-ገብነቶች (attendance interventions) - መደበኛ-አሰራር ላይ፣ Section F, ውስጥ እንደተገለጸው፣ የAC/AD በተጨማሪ - የደህናማ-መሆን ምልከታ-ማድረጊያ የስል ጥሪ (phone call)ን - ተማሪው ወደ ሦስት (3) ፈቃድ ያላገኘ በትምህርት ገበታ ላይ አለመገኘት (unexcused absences) ላይ ሲደርስ፤ ማንኛውም ቴኪኒካል እንቅፋቶች መኖራቸውን ለመለየት ወይም ሌላ አስቸጋሪ የሆኑ ነገሮች ገጥመው ከሆነ የሚከታተል እና የስልክ ጥሪው (phone call)ን ውጤት በአስፐን የግንኙነት ጆርናል (Aspen communication journal) ላይ በመዝገብነት-ያስቀምጣል።

---

51 የDCPS የኦፖርቹኒቲ አካዳሚስ (opportunity academies)፤ (ለምሳሌ፤ Roosevelt STAY, Luke C. Moore) በአካል-ተገኝቶ (in-person) እንቅስቃሴዎችን - እንዲሰጣቸው ለጠየቁ-ተማሪዎች መስጠት አለበት፤ ነገር-ግን ተማሪዎች የርቀርት (virtual) መማርን ሊመርጡ-የሚችሉ እና ይህን ለማድረግ የህክምና ሰርቲፊኬት ሂደት መስፈርትን-ማሟላት አያስፈልጋቸውም።

52 5-A DCMR § 2101.12.

53 5-A DCMR § 2101.13.